# እጥር ምጥን ያለ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ

# እና

# ለየት ያሉ አበይት መገለጫ ባህሪዎቻቸው


**هيثم بن محمد سرحان**

**ዝግጅት፡-**

**ሸይኽ ሀይሠም ኢብን ሙሐመድ ሰርሓን**

**በመስጂድ አን-ነበዊ ውስጥ የቀድሞ አስተማሪ**

**እና የዚህ ድረ ገፅ ዳይሬክተር፡-**

www.alsarhaan.com


غفر الله له ولوالديه ولمن أعانه على إخراج هذا الكتاب

አላህ ለርሳቸው፣ ለወላጆቻቸውና ይህን መጽሐፍ በማሳተም ረገድ ላገዟቸው አካላት ምሕረቱን ይለግሳቸው!

*ትርጉም፡-*

አቡ የሕያ (አሊ አማኖ)

الطَّبعة الأولى

جميع الحقوق محفوظةٌ
إلا لمن أراد طبعه أو ترجمته وتوزيعه مجَّاناً بعد مراجعة المؤلف

الرَّجاء التَّواصل على:

**islamtorrent@gmail.com**

فسح وزارة الإعلام

# መግቢያ

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ሁሉ ለኃያሉ አላህ የተገባ ይሁን፡፡ እርሱን እናመሰግነዋለን፤ በርሱም እንታገዛለን፤ ምሕረቱንም እንለምነዋለን፤ ከነፍሶቻችን ክፋቶችና ከመጥፎ ሥራዎቻችን ውጤትም በርሱ እንጠበቃለን፡፡ አላህ የመራውን ሰው ማንም አያጠመውም፡፡ እርሱም በጥመት ላይ የተወውን ሰው ለርሱ አቅኚ የለውም፡፡ ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም እመሰክራለሁ፡፡ እርሱም ብቸኛና አጋር የለሽ ነው፡፡ ሙሐመድም የአላህ ባሪያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት፡፡ እናንተም ሙስሊሞች ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ፡፡» (ኣሉ ዒምራን 3፡102)*

*«እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርሷም መቀናጀዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን፣ ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡» (አን-ኒሳእ 4፡1)*

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡ ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና፡፡ ኀጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል፡፡ አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ፡፡» (አል-አሕዛብ 33፡70-71)*

ከዚህም በመቀጠል ለዚያ የራሱን ነብይ ከታሪካቸውና ከምሪታቸው አነስተኛውን ነገር ማወቅ እርሱ ዘንድ ዝቅተኛው ሐሳብ ለሆነበት ሰው ሁሉ እነርሱን ከማወቅ የማይብቃቃባቸው እነዚህ ቀላል ቃላት ቀርበውለታል፡፡ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክና ምሪታቸውን የማወቅን አንገብጋቢነት አስመልክቶ ታላቁ ሊቅ ኢማም ኢብኑል ቀይም (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- «በሁለቱም ሀገራት ውስጥ የአንድ የአላህ ባሪያ ደስታው ከነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ምሪት ጋር የተቆራኘ እስከሆነ ድረስ፣ በዚያ ለነፍሱ መልካምን ነገር ለሚሻ፣ ድነቷንና ደስታዋንም ለሚወድ ሰው ሁሉ ከርሳቸው ምሪት፣ ከታሪካቸውና ከጉዳያቸው (የሚገባውን ያህል) ማወቅ በርሱ ላይ ግዴታ ይሆንበታል፡፡

በዚህም (ዕውቀቱ) ሳቢያ ከዚህ ጉዳይ አላዋቂዎች ከሆኑት ሰዎች መካከል ይወጣበታል፤ በዚህም አማካኝነት ከተከታዮቻቸው፣ ከደጋፊዎቻቸውና ከፓርቲያቸው ተርታ ይገባበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሰዎች አነስተኛ ዕውቀትን ብቻ የተሰጡ፣ ብዙ ዕውቀትን የተሰጡና (ከዚህ ዕውቀት ምንም ድርሻ) የሌላቸው በሚል መካከል ይካፈላሉ፤ ምክንያቱም ትርፋቱ በአላህ እጅ ሲሆን፣ እርሱም ትሩፋቱን ለሚሻው ሰው ይሰጣል፤ አላህም የታላቅ ትሩፋት ባለቤት ነውና፡፡

ልዕለ ኃይሉ አላህ እኔንና እናንተንም የነብዩን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ውዴታ፣ ያዘዙትን ነገር መታዘዝንና ከከለከሉት ነገር መራቅንና መገሰጽን እንዲለግሰን እማፀነዋለሁ፡፡ አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ እዝነትህን አስፍን፤ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ እንዳሰፈንክ ሁሉ፡፡ አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን አስፍን፤ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ፤ አንተ ምስጉኑና ልዑሉ ነህና፡፡ ምስጋና ሁሉ የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ይሁን፡፡

# ክፍል ፣፡ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መገለጫ ባህሪያት እና ምሪታቸው

# መገለጫ ባህሪዎቻቸው

## የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዘር ሐረግ

ስማቸው ሙሐመድ ኢብን ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል ሙጧሊብ ኢብን ሃሺም ኢብን ዐብዱ መናፍ ኢብን ቁሰይ-ዪ ኢብን ኪላብ ኢብን ሙር-ረህ ኢብን ከዕብ ኢብን ሉአይ-ዪ ኢብን ጋሊብ ኢብን ፊህር ኢብን ማሊክ ኢብን አን-ነድር ኢብን ኪናነህ ኢብን ኹዘይመህ ኢብን ሙድሪከህ ኢብን ኤሊያስ ኢብን ሙደር ኢብን ነዛር ኢብን መዐድ-ዲ ኢብን አድናን ሲሆኑ፣ አድናንም የኢስማዒል አዝ-ዘቢሕ ልጅ ናቸው። ኢስማዒልም የኢብራሂም አል-ኸሊል (ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በጥቅሉ በዘር ሐረጋቸው ረገድ ከመላው የምድር ነዋሪዎች መካከል እጅግ ምርጡ ናቸው። በሐዲሥም እንደተዘገበው የሮማው ንጉሥ ሂረቅል ለአቢ ሱፍያን እንዲህ ብሏቸዋል፦ «ስለዘር ሐረጉ ጠየቅኩ። አንተም እርሱ በዘር ሐረጉ ረገድ ከናንተ መካከል ምርጡ እንደሆነ አወሳህልኝ። ልክ እንደዚሁ መልዕክተኞች ከሕዝቦቻቸው መካከል ከምርጡ የዘር ሐረግ ይላኩ ነበር።»

## አላህ መረጣቸው

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «በእውነቱ አላህ ከኢስማዒል ልጆች መካከል ኪናናን መርጧል፣ ከኪናና ልጆች መካከልም ቁረይሽን መርጧል፣ ከቁረይሽም መካከል የሃሺም ልጆችን መርጧል፣ እኔንም ከሃሺም ልጆች መካከል መርጦኛል።» (ሙስሊም)

## የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች

ሁሉም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች መገለጫዎች እንጂ ለትውውቅ ብቻ የሚያገለግሉ ስሞች አይደሉም። ይልቁንስ እነርሱ ውዳሴና ምሉዕነት ከሚገባቸው ከተረጋገጡ መለያ ባህሪዎቻቸው የተገኙ ስሞች ናቸው።

### ሙሐመድ

ይህ ከርሳቸው ስሞች መካከል እጅግ ታዋቂው ነው። ይህ ስም በተውራት (ኦሪት) ውስጥም በግልጽ የተጠሩበት ነው። ትርጓሜውም የተመሰገነ፣ እርሱ ያ ለብዙ መልካም ባህሪያቱ የተወደሰ ማለት ነው።

### አሕመድ

ይህም ከፍጥረታት መካከል አላህን እጅግ ሲበዛ የሚያመሰግነው ወይም አመስጋኙ ማለት ነው። በመለያ ባህሪዎቻቸው ብዛት የተነሳ የሰማያትና የምድር ነዋሪዎች፣ የዱንያና የአኺራ ነዋሪዎችም ያመሰግኑታል (ያወድሱታልም)። ይህ አል-መሲሕ ዒሳ (ዐ.ሰ) እርሳቸውን የጠሩበት ስማቸውም ነው።

### አል-ሙተወክ-ኪል

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ስም የተጠሩበት ምክንያት ዲኑን በማቋቋም ረገድ ማንም የማይጋራቸውን ትክክለኛ ተወክ-ኩልን (በአላህ ላይ መመካትን) በአላህ ላይ በመመካታቸው ነው።

## የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች

| | |
|---|---|
| አል-ማሒ (አስወጋጁ) | አል-ማሒ ማለት ያ በእርሱ አማካኝነት ኃያሉ አላህ ክህደትን የሚያስወግድበት ማለት ነው። ስለሆነም ኃያሉ አላህ በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት ክህደትን ባስወገደበት ልክ በሌላ በማንም አማካኝነት አላስወገደም። |
| አል-ሓሽር (ሰብሳቢው) | አል-ሓሽር ማለት እርሱ ያ መላው የሰው ዘር በርሳቸው እግር ሥር የሚሰባሰብለት ማለት ነው። ይህም ልክ እርሳቸው የሰውን ልጆች ለማሰባሰብ እንደተላኩት ዓይነት ነው። |
| አል-ዓቂብ (የመቋጫው) | አል-ዓቂብ (የመደምደሚያው) ማለት እርሱ ያ ከኋላው ሌላ ነብይ የማይመጣበት ማለት ነው። ስለሆነም እርሳቸው የነብያት ሁሉ መቋጫ ናቸው። |
| አል-ሙቀፍ-ፊ (ዱካን ተከታዩ) | አል-ሙቀፍ-ፊ ማለት እርሱ ያ የቀደሙትን (ነብያት) ዱካን ተከትሎ የተላከ ማለት ነው። ኃያሉ አላህም ከመልዕክተኞች እርሳቸውን በቀደሙት ዱካ ላይ ተከታይ አድርጎ ላካቸው። |
| ነብዩት-ተውባ | የተውበቱ ነብይ ማለት ያ በርሱ አማካኝነት አላህ ለምድር ነዋሪዎች የተውበትን በር የከፈተበት ሲሆኑ (ተከታዮቻቸውም) ከርሳቸው በፊት ማንም ያላገኘውን ተውበትን (በማግኘት አላህም ፀፀታቸውን ተቀብሎ በምሕረቱ) ተመለሰላቸው። እናም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው ተውበት ማድረግንና ምሕረት መለመንን ከሚያበዙ ሰዎች ሁሉ በላጩ ናቸው። |
| ነብዩል መልሐማ | ነቢይ-ዩል መልሐማ (ጀግናው ነብይ) ማለት ያ የአላህን ጠላቶች እንዲታገል የተላከ ጀግና ማለት ነው። ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው በአላህ መንገድ ላይ በታገሉት ልክ የታገለ ሌላ ነብይና ተከታዮቹ የሉም። እነዚያ የተሰው ታላላቅ ጀግኖችም ከርሳቸው በፊት ፈፅሞ እንደሚነሱ ቃል አልተገቡም ነበር። |
| ነብዩር-ረሕማ | ነቢይ-ዩል መልሐማ (ጀግናው ነብይ) ማለት ያ የአላህን ጠላቶች እንዲታገል የተላከ ጀግና ማለት ነው። ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው በአላህ መንገድ ላይ በታገሉት ልክ የታገለ ሌላ ነብይና ተከታዮቹ የሉም። እነዚያ የተሰው ታላላቅ ጀግኖችም ከርሳቸው በፊት ፈፅሞ እንደሚነሱ ቃል አልተገቡም ነበር። |
| አል-ፋቲሕ (ከፋቹ) | አል-ፋቲሑ ማለት ያ አላህ ምሪትን (የቅናቻ መንገድን)፣ እርሱ ከተወዛወዘ በኋላ የከፈተበት ነው። የዕውሮችን ዓይኖች፣ የደንቆሮዎችን ጆሮዎችና የተሸፈኑ ልቦችን የከፈተበት ነው። እንደዚሁም በርሳቸው አማካኝነት ኃያሉ አላህ የከሀዲዎችን ግዛቶች ከፈተበት። በርሳቸው አማካኝነትም የጀነትን በሮች ከፈተበት። እንደዚሁም ወደጠቃሚ ዕውቀትና ወደ መልካም ሥራ (የሚያደርስ) መንገድን ከፈተበት። |

## የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች

**አል-አሚን (ታማኙ)**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዓለማት እንደዚህ ዓይነት ስም ይኖራቸው ዘንድ እጅግ ተገቢው ሰው ናቸው፡፡ በወሕዩ እና በዲኑ ረገድ በአላህ ዘንድ ታማኙ ሰው ናቸው፡፡ እርሳቸው በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድም ታማኙ ናቸው፡፡ በምድር ነዋሪዎች ዘንድም ታማኙ ናቸው፡፡ እንዲያውም መልዕክተኛ ሆነው ከመላካቸው በፊት የቁረይሽ ከሀዲያን እርሳቸውን ‹አል-አሚን› በማለት መሰየማቸው የሚታወስ ነው፡፡

**አል-በሺር (አብሳሪው)**

አል-በሺር ማለት እርሱ ያ እርሳቸውን የሚታዘዙ ሰዎች ታላቅ ምንዳን በማግኘት የሚያበስሩና እርሳቸውን የሚያምፁትን ደግሞ በቅጣት የሚያስጠነቅቁ ናቸው፡፡

**የአደም ልጆች ሁሉ አለቃ**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ በትንሳኤው ዕለት የኣደም ልጆች ሁሉ አለቃ ነኝ፤ ይህም ጉራ አይደለም .... »

**አስ-ሲራጅ አል-ሙኒር (አንፀባራቂ ደማቅ ብርሃን)**

አስ-ሲራጅ አል-ሙኒር ማለት ያ ሳያቃጥል ደማቅ ብርሃንን የሚያስገኝ ነው፡፡ ይህም ከወሀ-ሃጅ ተቃራኒ መሆኑ ነው፤ ምክንያቱም በወሀ-ሃጅ ውስጥ አቃጣይ የሆነ የብርሃን ዓይነት አለበትና፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዐብዱሏህ ናቸው፡፡ ትርጉሙም የአላህ ባሪያ ሲሆን ዒባዳ ሁሉ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው፡፡ ዐብዱሏህ የተባሉበት ሁሉንም የዒባዳ ደረጃዎችን ስላማሉ ነው፡፡

## ውብ መገለጫዎቻቸው

የነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እጅግ የተሟላ መግለጫያቸው እርሳቸው ራሳቸውን የገለጹበት መንገድ ነው፡፡ እንዲህም ብለዋል፡-

*«እኔ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው ሙሐመድ ነኝ፡፡ (ስለሆነም ልዕለ ኃያሉ) አላህ እኔን ካስቀመጠበት ደረጃ በላይ እናንተ ከፍ እንድታደርጉኝ አልወድም፡፡»*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአፈጣጠርና በምግባር ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ ናቸው፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡»* (68፡4)

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ምግባራቸው ቁርኣን ነበር፡፡» ስለሆነም በቁርኣኑ ይሠሩበት፤ ሕግጋቱም ጋር ይቆሙ፤ የሚወደውንም ይወዱና በሚያስከፋውም ይከፉ ነበር፡፡

**የአላህ ወዳጅ**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእውነቱ አላህ ልክ ኢብራሂምን ወዳጁ አድርጎ እንደያዛቸው ሁሉ እኔንም ወዳጁ አድርጎ ይዞኛል፡፡»

## የአፈጣጠራቸው መገለጫዎች

**ከቡር ገላቸው**

አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡-

«የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ደማቅ የሆነ (የፊት) ቀለም ያላቸው ነው፤ (ማለትም ነጭና ከብ) መልክ አላቸው፡፡ የላቦታቸው (ጠብታዎች) ልክ እንደ ሉል (የሚያንፀባርቁ) ናቸው፡፡ በሚራመዱበትም ጊዜ ወደፊት አዘምመው ነው፡፡ እኔ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መዳፍ ይበልጥ ለስላሳ የሆነ ዲባጅንም (ከሐር የበለጠ ውድ ልብስ) ሆነ ሐርንም አልነካሁም፡፡ እንደዚሁም እኔ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጠረን የበለጠ ምርጥ መዓዛ ያለው ሚስክም ሆነ ዐንበር አሽትቼ አላውቅም፡፡»

## የአፈጣጠራቸው መገለጫዎች

| | |
|---|---|
| ተክለ ቁመናቸው | አል-በራእ ኢብን ዓዚብ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሀከለኛ ቁመት አላቸው (ረጅምም አጭርም አይደሉም)፡፡ በሁለቱ ትከሻዎቻቸው መካከል ያለው ቦታም ሰፊ ነው፡፡ እስከ ጆሮአቸው የሚደርስ ፀጉርም አላቸው፡፡ ቀይ ሙሉ ልብስ ለብሰው አይቻቸዋለሁ፡፡ ከርሳቸው ይበልጥ ያማረ አንዳችም ነገር ፈፅሞ አይቼ አላውቅም፡፡» |
| ፊታቸው | ከዕብ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(አንድ ቀን) ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታን ሳቀርብ ከደስታ የተነሳ ፊታቸው ያብረቀርቅ ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ደስተኛ በሆኑ ጊዜ ፊታቸው ልክ እንደ ጨረቃ ቁራሽ ያበራ ነበር፡፡ ስለሆነም እኛም ይህንኑ ከፊታቸው ላይ እናውቅ ነበር፡፡»<br><br>እንደዚሁም አል-በራእ «የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊት ሰይፍን ይመስል ነበር ወይ?» ተብለው ተጠይቀው ነበር፡፡ እርሳቸውም «የለም! ይልቁንስ ፊታቸው ጨረቃን ነው የሚመስለው» በማለት መለሱ፡፡ |
| ፀጉራቸው | አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ትላልቅ እጆች አላቸው፡፡ እኔም ከርሳቸው በኋላ የርሳቸውን እጆች የሚመስል (እጅ) ፈጽሞ አይቼ አላውቅም፡፡ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፀጉር ያልተረጋጋ ሲሆን የተጠቀለለ ፀጉርም አይደለም፤ ቀጥ ብሎ የቆመም አይደለም፡፡» |
| ዓይኖቻቸው | ጃቢር ኢብን ሰሙረህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሰፊ አፍና ቀያይ (ሰፋፊ) ዓይኖች (በነጫጭ ዓይኖች ውስጥ ቅላት ያለበት) እና ቀጫጭን ተረከዞች አላቸው፡፡ |
| ላባቸው | አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደቤታችን ገቡና እኛም ዘንድ ቀይሉላን (በቀኑ ክ/ጊዜ የሚተኛውን እንቅልፍ) ተኙ፡፡ ላብም አላባቸው፡፡ እናቴም ብልቃጥ ይዛ መጣችና (ላባቸውን ወደዚያ) አንቆረቆረች (ወይም በዕቃው ውስጥ) ላቦቱን ሰበሰበች፡፡ (የኋላ ኋላም) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንቅልፋቸው ነቁና ‹ኡም-ሡ ሰለይም ሆይ! ምን እያደረግሽ ነው?› አሏት፡፡ እርሷም ‹ይህ የርስዎ ላብ ነው፤ በሽቶአችንም ውስጥ እናደርገዋለን፤ እርሱም ከሽቶዎች ሁሉ በላጩ ሽቶ ይሆናል› አለች፡፡» |
| የነብይነት ማሕተማቸው | ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በትከሻዎቻቸው መካከል የነብይነት ማሕተም አለባቸው፡፡ ይህም ልክ እንደ ልደት ምልክት በሰውነታቸው ላይ የሚገኝ አንዳች ለየት ያለ ነገር ነው፡፡<br><br>ጃቢር ኢብን ሰሙረህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «ትከሻቸው ላይ የፔንጊዮን እንቁላልን የሚመስል ማሕተም አየሁ፡፡ ከሰውነታቸው (የቆዳ ቀለም) ጋርም ይመሳሰላል፡፡» |

## የምግባራቸው መገለጫዎች

### ባልደረቦቻቸው ለርሳቸው የነበራቸው አክብሮት

ዐምር ኢብን አል-ዓስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በላይ እኔ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ሰው የለም፤ ከርሳቸውም በላይ በዓይኖቼ ዘንድ የላቀ ሰው የለም፤ ለርሳቸው ካለኝ አክብሮት የተነሳ በሙሉ ዓይኖቼ ልመለከታቸው ዘንድ ድፍረቱ አልነበረኝም፡፡ ስለሆነም እርሳቸውን እንድገልጻቸው ብጠየቅ፣ ያንኑ ማድረግ አልችልም፤ ምክንያቱም በሙሉ ዓይኖቼ እርሳቸውን አይቻቸው አላውቅምና፡፡»

ዑርዋ ኢብን መስዑድ አሽ-ሸቀፊይ-ይ (ረ.ዐ) በሑደይቢያው (ስምምነት) ዕለት እርሳቸውን ለቁረይሾች በሚገልጽበት ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡- «በአላህ እምላለሁ! የሙሐመድ ባልደረቦች ሙሐመድን እንደሚያከብሩት ባልደረቦቼ (የክብር ባለሟሎቼ) ዘንድ እንደዚያ የሚከበር ንጉሥ አላየሁም፡፡ በአላህ እምላለሁ! እርሳቸው አንዲት ምራቅን የተፉ እንደሆነ፣ ምራቁ ከነርሱ (ከነብዩ ባልደረቦች) መካከል በአንዳቸው መዳፍ ላይ የሚያርፍ ቢሆን እንጂ አይተፉም ነበር፡፡ እርሱም በዚያ (ምራቅ) ፊቱንና (የሰውነቱን) ቆዳ ያብስበታል፡፡ አንዳች ነገርን ባዘዛቸው ጊዜም ትዕዛዛቸውን ለመፈጸም ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡ እርሳቸው ዉዱእ ያደረጉ እንደሆነ፣ የተቀረውን ውሃ ለመውሰድ ሲሉ እርስ በርሳቸው ለመታገል ይቀርቡ ነበር፡፡ እርሳቸው በሚናገሩበት ጊዜ፣ ከርሳቸው ዘንድ ድምፃቸውን ዝቅ ያደርጉ ነበር፡፡ ለርሳቸው ካላቸው አክብሮት የተነሳም ወደርሳቸው ፊት በቀጣይነት አይመለከቱም ነበር፡፡»

### ከአላህ ጋር የነበራቸው አዳብ

ዐብዱል-ሏህ ኢብን አሽ-ሺኽ-ኺር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን እኛ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)) ‹እርስዎ አለቃችን (ሰይ-ዪዳችን) ነዎት› አልናቸው፡፡ እርሳቸውም «አለቃው የተባረከውና የተላቀው አላህ ነው» አሉ፡፡ እኛም «እርስዎ በላጫችንና በልግስናም ረገድ ታላቃችን ነዎት» አልናቸው፡፡ እርሳቸውም «ማለት የሚገባችሁን ነገር ብቻ በሉ፤ ወይም ማለት ከሚገባችሁ ነገር ከፊሉን በሉ፤ ሸይጣንም (ከመንገዳችሁ ላይ) እንዳያሮጣችሁ አደራችሁን (ተጠንቀቁ)› አሉን፡፡»

### ጀግንነታቸው

ዐሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ጦርነቱ በሚፋፏምበትና ሁለቱም ጎራዎች ለውጊያ ግንባር ለግንባር በሚገናኙበት ጊዜ እኛ ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንጠለላቸው ነበር፤ (ምክንያቱም) ከኛ መካከል የርሳቸውን ያህል ወደሰዎቹ (ወደጠላት) የሚቀርብ አንድም ሰው የለምና ነው፡፡»

### ለአላህ የነበራቸው ፍራቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «... በአላህ እምላለሁ! እኔ ከናንተ መካከል ይበልጥ አላህን ፈሪውና ከናንተም በላይ ይበልጥ ከርሱ ተጠንቃቂው ነኝ፡፡ ....»

### ለቤተሰባቸው ያላቸው ደግነት

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «ከናንተ መካከል ምርጡ ለቤተሰቡ (ለሚስቱ) ይበልጥ ምርጡ የሆነው ሰው ነው፡፡ እኔም ከናንተ መካከል ለቤተሰቦቼ ይበልጥ ምርጡ ነኝ፡፡»

### ዓይና-ፋርነታቸው

አቡ ሰዒድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በዓይናፋርነት ረገድ በጓዳቸው ውስጥ ካሉ ልጃ ገረዶች ይበልጥ ብርቱ ናቸው፡፡ አንዳች የሚጠሉትንም ነገር በተመለከቱ ጊዜ፣ ያንኑ ከፊታቸው ላይ እናውቅ ነበር፡፡»

### ማግራራ-ታቸው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሁለት ጉዳዮች መካከል ምርጫን አያደርጉም ነበር፤ ይበልጥ ገር የሆነውን ነገር የመረጡ ቢሆን እንጂ፤ ያ ነገር ኃጢአትን የማያስከትል እስከሆነ ድረስ፡፡ ጉዳዩ (ኃጢአት ከሆነ) ግን፣ ከማንም በላይ ከሁለቱም (አማራጮች) ይበልጥ የሚርቁ ነበሩ፡፡»

## የምግባራቸው መገለጫዎች

**ለራሳቸው ብለው አልተበቀሉም**

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «በአላህ እምላለሁ! የአላህ ክልከላዎች እስካልተጣሱ ድረስ (ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/) ወደርሳቸው ለመጣው በማንኛውም ነገር ለራሳቸው ብለው የበቀል እርምጃ ወስደው አያውቁም፡፡ (ነገር ግን) ለአላህ ብለው የበቀል እርምጃን ይወስዱ ነበር፡፡»

**ምግብን አናውረው አያውቁም**

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ምግብን አነውረው (ለምግብ አቃቂር አውጥተው) አያውቁም፡፡ (ይልቁንስ) የወደዱት እንደሆነ ይመገቡት፣ የጠሉት እንደሆነ ደግሞ ይተውት ነበር፡፡»

**ስጦታን ይቀበሉ ነበር**

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ስጦታን ይቀበሉና በአጸፋውም አንዳች ነገርን ይሰጡ ነበር፡፡»

**ምጽዋትን ተቀብለው አያውቁም**

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «የሙሐመድ ቤተሰቦች ከሰደቃ (ከምጽዋት) አይመገቡም፡፡»

**ትሕትናቸው**

ዑቅባ ኢብን ዓሚር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን) አንድ ሰውዬ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና አናገራቸው፡፡ በሚያወራበት ጊዜም (ከአክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ) በደረቱና በትከሻዎቹ መካከል ያለው የሰውነት ክፍሉ በኃይለኛው ይንቀጠቀጥ (ይመታ) ነበር፡፡ (በዚህን ጊዜ) ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ‹ተረጋጋ፤ ምክንያቱም እኔ ንጉሥ አይደለሁምና፡፡ በእውነቱ እኔ የዚያች ድርቆሽ (ተምር) የምትበላ ሴት ልጅ ብቻ ነኝ› አሉት፡፡»

**ቤተሰባቸውን ማገልገላቸው**

ከአል-አስወድ ኢብን የዚድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንደተወራው እኔ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በቤታቸው ውስጥ ምን እንደሚሠሩ ዓኢሻን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጠየቅኳቸው፡፡ እርሷም «በቤተሰቦቻቸው አባላት ሙያ ላይ ይሆኑ ነበር - የቤተሰቦቻቸውን አባላት በመስተንግዶ ያግዙ ነበር፡፡ ሶላትም በደረሰች ጊዜ ወደ ሶላት ይወጡ ነበር» አለች፡፡

**አላዋቂዎችን ችላ ማለታቸው**

የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «ኃያሉ አላህ የቁረይሾችን ስድብና እርግማናቸውን ከኔ ላይ እንዴት እንደመለሰ (ብታውቁ) አያስደንቃችሁምን? እነርሱ ሲሰድቡ የነበረው ሙዘም-መምን ነው፡፡ ሲረግሙትም የነበረውም ሙዘም-መምን ነው፤ ይሁንና እኔ ሙሐመድ ነኝ (እንጂ ሙዘም-መም አይደለሁም)፡፡»

**እውነተኛ-ነታቸው**

ዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የእውነተኞች ሁሉ እውነተኛ የሆኑት የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) (እንደዚያና እንደዚህ) ብለው ነግረውናል፡፡›

**ከአገልጋዮቻቸው ጋር የነበራቸው ምግባር**

አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ የአላህን መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ለአስር ዓመታት ያክል አገልግያቸዋለሁ፤ እርሳቸውም ለኔ (አንድም ቀን ፈጽሞ) ‹ኡፍ-ፍ› (ውድቅ የማድረጊያ ቃል) ብለውኝ አያውቁም፡፡ እንደዚሁም ለአንዳች እኔ ለሠራሁት ነገር ‹እንዲህ ለምን አደረግክ?› ብለውኝ አያውቁም፡፡ እንደዚሁም አንዳች እኔ ያልሠራሁትን ነገር አስመልክቶም ‹እንደዚህ አላደረግኸምን?› ብለውኝ አያውቁም፡፡»

# የምግባራቸው መገለጫዎች

## ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ለየት ብለው አያውቁም

አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኛ በመስጊድ ውስጥ ተቀምጠን ሳለ በግመል ላይ የተቀመጠ ሰው ገባና ግመሉም በመስጊዱ ውስጥ እንዲንበረከክ አደረገ፡፡ ከዚያም ግመሉን አሰረውና ለነርሱም ‹ከናንተ መካከል ሙሐመድ የትኛችሁ ነው?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው በስተ ጀርባ ጋደም ብለው ተቀምጠው ነበር፡፡ እኛም ለሰውዬው ‹ይህ ጋደም ብሎ የተቀመጠ ነጩ ሰውዬ ነው› አልነው፡፡ ሰውየውም ለርሳቸው ‹አንቱ የዐብዱል ሙጠሊብ ልጅ ሆይ!› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹አቤት ብያለሁ› አሉት፡፡ ሰውዬውም ‹ሙሐመድ ሆይ! እኔ ጥያቄዎችን ልጠይቅህ ነው፤ በአጠያየቄ ውስጥም ኃይለኛ እሆንብሀለሁ፤ ስለሆነም እንዳትከፋብኝ› አላቸው፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹የተገለጠልህን ነገር ጠይቅ› አሉት፡፡ ሰውዬውም «እኔ ባንተና በነዚያ ካንተ በፊት በነበሩ ሰዎች ጌታ ስም እማጸንሀለሁ፤ ለመሆኑ አንተን ወደመላው የሰው ልጆች የላከህ አላህ ነውን?» አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን› አሉት፡፡ እርሱም ‹እኔ በአላህ ስም እማፀንሀለሁ፤ በእያንዳንዱ ቀንና ሌሊት አምስት ወቅት ሶላቶችን እንድንሰግድ ያዘዘን አላህ ነውን?› አላቸው፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡ እርሱም ‹እኔ በአላህ ስም እማፀንሀለሁ፤ ከዓመቱ ውስጥ ይህንን ወር እንድንፆም ዘንዳ ያዘዘን አላህ ነውን?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡ እርሱም ‹በአላህ ስም እማፀንሀለሁ! ይህንን ዘካት ከሀብታሞቻችን እንድትወስድና በድሆቻችንም መካከል እንድታከፋፍል ያዘዘህ አላህ ነውን?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡

ሰውዬውም ‹እኔ አንተ ይዘህ በመጣኸው ነገር አምኛለሁ፤ እኔም ከኔ ኋላ ላሉ ሕዝቦቼ መልዕክተኛቸው ነኝ፤ እኔ ዲማም ኢብን ሠዕለባ፣ የበኑ ሰዐድ ኢብን በክር ወንድም ነኝ› አለ፡፡»

## ምግባቸው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)» ቤተሰቦች ለሁለት ተከታታይ ቀናት ከገብስ የተሠራ ዳቦን ጠግበው በልተው አያውቁም፡፡

## በዱኒያ ውስጥ የነበራቸው ዙህድ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከዚህ ከኡሑድ (ተራራ) ጋር የሚስተካከል ወርቅ ቢኖረኝ አያስደስተኝም፤ ከርሱ የሆነ ምንም ነገር - ከርሱ የሆነ አንዲት ዲናር እንኳ ሳይቀር - ዕዳን ለመክፈል ከማስቀረው ነገር በስተቀር እኔ ዘንድ ከሦስት ቀናት በላይ መቆየቱ አያስደስተኝም፤ (ይልቁንስ) እርሱን በአላህ ባሮች መካከል ልክ እንደዚህ፣ ልክ እንደዚህ እና ልክ እንደዚህ እያልኩ (የማከፋፍለው) ብሆን እንጂ፡፡»

## ፀያፍ ቃላትን አልተናገሩም

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባለጌም አይደሉም፡፡ የብልግና ቃላትንም የሚናገሩ አይደሉም፡፡ በገበያ ቦታዎች ውስጥም ጮኽ ብለው የሚያወሩ አይደሉም፡፡ ለመጥፎ ሥራ በመጥፎ ሥራ አማካኝነት አጸፋ ሰጥተው አያውቁም፡፡ ይልቁንስ ይቅርታን ያደርጉና ባላየ ያልፉ ነበር፡፡»

## የባዳ ሴትን እጅ ነክተው አያውቁም

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- « ... የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እጆች የባዳ ሴትን መዳፍ ፈፅሞ ነክተው አያውቁም፡፡»

የምግባራቸው መገለጫዎች

የአኗኗራቸው ሁኔታ

ዑመር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከቄጠማ የተሠራ ሰሌን ላይ ሳሉ በርሳቸው ላይ ገባሁና ተቀመጥኩ፡፡ሽርጣቸውም ተጣብቆባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭም ሌላ ነገር በርሳቸው ላይ የለም ፡፡ስለሆነም የቄጠማው ምንጣፍ በጎናቸው ላይ ምልክቶችን አሳርፏል፡፡ በዓይኔም ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዕቃ ቤት ተመለከትኩ፡፡ በዚህን ጊዜ አንድ እፍኝ፣ ከሞላ ጎደል አንድ ሷዕ የሚሆን ገብስ ተመለከትኩ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የተወሰኑ የግራር ቅጠሎችን በክፍሉ ጥግ ላይ ተመለከትኩ፡፡ እንደዚሁም የተንጠለጠለ ሌጦም (ተመለከትኩ)፡፡ ዓይኖቼ በእንባ ተጥለቀለቁ፡፡ እርሳቸውም ‹የአል-ኸጧብ ልጅ ሆይ! ምንድነው የሚያስለቅስህ?› አሉኝ፡፡ እኔም ‹የአላህ ነብይ ሆይ! ለምንድነው የማላለቅሰው? ይህ ሰሌን እኮ በርስዎ ጀርባ ላይ ሰንበርን አሳርፏል፤ እርስዎ ያከማቹት ነገር ሁሉ ይህ ብቻ ነው፡፡ በዚህች (የዕቃህ) ክፍልህ ውስጥ ከማየሁ ነገር ውጭ ሌላ አንዳችም ነገር ማየት አልቻልኩም፡፡ ከወደዚያ ቄሰርና ኪስራ (ንጉሦቻቸው) በፍራፍሬዎችና በወንዞች ውስጥ (የሚንደላቀቁ ናቸው)፡፡ ይሁንና እርስዎ የአላህ መልዕክተኛና የርሱ ተመራጩ ሰው ነዎት፤ እናም እርስዎ ያከማቹት ነገር ይኼው ነው?› አልኳቸው፡፡ እርሳቸውም ‹የአል-ኸጧብ ልጅ ሆይ! ለመሆኑ ኣኺራ ለኛ ብትሆንና ዱንያም ለነርሱ ብትሆን አትደሰትምን? (ማለትም እነዚህ ነገሮች በቀጣዩ ዓለም ለኛ መሆናቸውና በዚህች ዓለም ውስጥ ደግሞ ለነርሱ መሆናቸውን (ማወቅህ) አያስደስትህም ወይ?› አሉኝ፡፡ እኔም ‹እንዴታ! (ያስደስቱኛል እንጂ)› አልኳቸው፡፡

# የመጀመሪያው ፈተና

| ውሸት | እውነት | ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| £ |  | የአንድ የአላህ ባሪያ ደስታው በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ውስጥ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምሪት ጋር የተቆራኘ ነው:: |
| £ | £ | መልዕክኞች የተላኩት ከሕዝቦቻቸው ምርጥ የዘር ሐረግ ነው፡ |
| £ | | የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምርጡ መገለጫ ቢኖር እርሳቸው «እኔ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው ሙሐመድ ነኝ» በማለት ራሳቸውን የገለጹበት መንገድ ነው:: |
| £ | £ | አላህ በመልዕክተኛው ዘንድ ሁሉንም የተሟሉ ምግባራትንና የተዋቡ መገለጫ ባህሪያትን አሰብስቧል:: ለርሳቸውም ከዕውቀትና ከትሩፋትም ሰጥቷቸዋል:: በዚህም ውስጥ በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ድል፣ ስኬትና ደስታ አለበት:: ይህ (ሁሉ ልቅናም) ከዓለማት ውስጥ ለሌላ ለአንድም ሰው አልተሰጠም:: |
| £ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያልተማሩ፣ ማንበብም ሆነ መጻፍ የማይችሉ፣ እንደዚሁም አንድም ሰብአዊ አስተማሪ ያልነበራቸው ሰው ናቸው:: |

1. በደፈናው በዘር ሐረግ ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ፡
   ሀ/ ዩኑስ ኢብኑ መት-ታ ለ/ ሙሐመድ ኢብን ዐብደላህ (ሰ.ዐ.ወ)
2. ስሞቻቸው፡- ሀ/ ሁሉም መገለጫዎች ናቸው ለ/ ለትውውቅ ብቻ የሚጠቅሙ ምልክቶች ናቸው ሐ/ ምስጋናንና ውዳሴን ከሚያስከትሉ የተረጋገጡ ባህሪያት የተገኙ ናቸው መ/ ሁሉም ሠ/ ሀ እና ሐ
3. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «ምግባራቸው ሁሉ ቁርኣን ነው» ማለት፡- ሀ/ ቁርኣኑን በሚያስደስት ነገር ይደሰቱ ነበር ለ/ ቁርኣኑን በሚያስቆጣ ነገር ይቆጡ ነበር ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
4. ኸሊሉሏህ (የአላህ ወዳጅ) ማነው? ሀ/ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ለ/ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሐ/ ሁለቱም
5. «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቆዳ ቀለማቸው በጣም ደመቅ ያለ ነው» ማለት፡- ሀ/ ስንዴያማ (ፈዘዝ ያለ ቢጫ) ለ/ ነጭ ሐ/ እጅግ የነጣ
6. ከሽቶዎች ሁሉ ምርጡ ሽቶ፡- ሀ/ ሚስክ ለ/ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላብ
7. «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቁመታቸው መሀከለኛ ነው» ማለት፡-
   ሀ/ ረጅምም አጭርም አይደሉም ለ/ ቁመታቸው ረጅም ነው
8. የነብይነት ማሕተማቸው፡- ሀ/ በትከሻዎቻቸው መካከል ይገኛል ለ/ ከሰውነታቸው ጋር ይመሳሰላል ሐ/ የፔንጊዮንን እንቁላል ይመስላል መ/ ሁሉም ልክ ነው

| ከቁረይሽ መካከል | ኢስማዒል | ከሃሺም ልጆች መካከል | ከኪናና | አላህ መረጠ፡- |
|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | ኪናናን ከ ....... ልጆች መካከል |
| £ | £ | £ | £ | ቁረይሽን ከ ........... |
| £ | £ | £ | £ | ከሃሺም ልጆች ............ |
| £ | £ | £ | £ | ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከ.......... |

| የቅመ ቅምቅመ አያታቸው ስም | የቅምቅመ አያታቸው ስም | የቅመ አያታቸው ስም | የአያታቸው ስም | የአባታቸው ስም | ስማ-ቸው | የዘር ሐረጋቸው፡- |
|---|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ሃሺም |
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ዐብዱል መጠሊብ |
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ዐብደሏህ |
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ሙሐመድ |
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ኢስማዒል |
| £ | £ | £ | £ | £ | £ | ኢብራሂም |

| አስ-ሲራጅ | አል-ዓቂብ | አሕመድ | ሙሐመድ | ቀጥሎ ያሉትን አዛምዱ፡- |
|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | ያ ጌታውን እጅግ አብዝቶ የሚያመሰግነው |
| £ | £ | £ | £ | ያ ያለ ማቃጠል ደማቅ ብርሃንን የሚሰጥ |
| £ | £ | £ | £ | ያ በርካታ ምስጉን ባህሪያት ያለው |
| £ | £ | £ | £ | ያ ከኋላው ነብይ የማይመጣበትና የነብያት ሁሉ መቋጫ የሆነው |

| አላህን በመፍራት | በአፈጣጠርና ምግባር | በአኗኗር | ጠረናቸው | መዳፎቻቸው | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| □ | £ | £ | £ | £ | ከሰዎች ሁሉ ምርጡ |
| □ | £ | £ | £ | £ | እጅግ ለስላሳ ናቸው |
| □ | £ | £ | £ | £ | እጅግ የሚያውድ ነው |
| □ | £ | £ | £ | £ | እጅግ ደግ ናቸው |
| □ | £ | £ | £ | £ | እጅግ የበረቱ ናቸው |

| ስጦታ | ምጽዋት | ለራሳቸው | ምግብ | ለአላህ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | ብለው አይበቀሉም |
| £ | £ | £ | £ | £ | ብለው ይበቀሉ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | አያነውሩም ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | ይቀበሉና አብዝተውም ይሰጡ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | አይቀበሉም ነበር |

# የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ

## አለባበስን፣ አመጋገብንና አጠጣጥን የሚመለከቱ መመሪያዎቻቸው

### እርሳቸው ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑ ከለሮች

ከከለሮች ሁሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የሆነው ነጭ ከለር ነው፡፡ ይህንኑ በማስመልከትም እንዲህ ብለዋል፡- «እርሷ (ነጭ ከለር) ከልብሶቻችሁ (ከለሮች) መካከል በላጩ ናት፤ ስለሆነም ሙታኖቻችሁን በርሷ (በነጭ ልብስ) ከፍኑ፡፡»

### አለባበሳቸው

አለባበሳቸውን በተመለከተ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመልበስ ቀላል የሆኑትን ልብሶች ይለብሱ ነበር፡፡ ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ ከሱፍ የተሠሩ ልብሶችን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከጥጥና ከላይነን የተሠሩ ልብሶችን ይለብሱ ነበር፡፡ እንደዚሁም ልብሳቸውን በሚለብሱበት ጊዜ ከቀኛቸው ይጀምሩ ነበር፡፡

### በአለባበስ መሀከለኛ መሆናቸው

ከቀደምቶቻችን መካከል አንዳንዶቻቸው እንዲህ ብለዋል፡- «እነርሱ (ሰለፎች) ሁለት ዓይነት ልብሶችን - ውድ የሆኑ የይዩልኝ ባይነት (የጉራ) ልብሶችንና ያረጁ ያፈጁ የሆኑ (የዛሂድነት ማሳያ የሚመስሉ ልብሶችን) - ይጠሉ ነበር፡፡» ከዐብዱሏህ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) በተወራው ሐዲሥ ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የይዩልኝ ባይነትን (የጉራን) ልብስን የለበሰ ሰው፣ አላህ በትንሳኤው ዕለት እርሱን የውርደት ልብስ ያለብሰዋል፡፡ ከዚያም በውስጡ እሳት ይቀጣጠልበታል፡፡» ይህም የሆነበት ምክንያት እርሱ (በልብሱ) በኩራትና እብሪት ለማጉረር አቅዶ ስለተነሳ ነው፡፡ ስለሆነም አላህ ለዚህ (ወንጀሉ) ቀጣው፡፡ እንደዚሁም ከኢብን ዑመር (ረ.ዐ) በተወራው መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ያ ከኩራት ተነሳ ልብሱን (ከቁርጭምጭሚቶቹ በታች አውርዶ) የሚጎትት ሰው፣ በትንሳኤው ዕለት አላህ ወደርሱ አይመለከትም፤ (ከወንጀሉም አያፀዳውም)፡፡»

### ምግባቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያገኙትን ነገር መመገብን እምቢ አይሉም ነበር፡፡ የሌለ ነገር እንዲሠራ በማድረግም ጫና አይፈጥሩም ነበር፡፡ ከንጹሕ ነገሮች አንዳችም ነገር አይቀርብላቸውም፤ የተመገቡት ቢሆን እንጂ፡፡ አንዳች በግላቸው የማይወዱት ነገር ሲሆን ግን፣ ያንኑ ነገር ሐራም ሳያደርጉት ይተውት ነበር፡፡እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፊፅሞ ለምግብ አቃቂር አውጥተው አያውቁም፡፡የወደዱት እንደሆነ ይመገቡት፣ አልያም ይተውት ነበር፡፡» ይህም ልክ የአርጃኖን ሥጋ መመገብን ክልክል ሳያደርጉት እንደተውት ነው፡፡

### የአመጋገብ ሁኔታቸው

- አብዛኛው ምግባቸው በሱፍራ ተደርጎ መሬት ላይ ይደረግ ነበር፡፡
- በሦስት ጣቶቻቸው አማካኝነት ይመገቡ ነበር፡፡
- ተጋድመው በመቀመጥ አይመገቡም ነበር፡፡
- በምግባቸው ጅማሮ ላይ የአላህን ስም ይጠሩ ‹ቢስሚሏህ› (በአላህ ስም) ይሉና በስተ መጨረሻም እርሱን ያመሰግኑት ‹አል-ሐምዱ ሊሏህ› (ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባ) ይሉ ነበር፡፡
- ምግባቸውን ከጨረሱ በኋላ ጣቶቻቸውን ይልሱ ነበር፡፡

### መጠጣቸው

- አብዛኛውን ጊዜ ተቀምጠው ይጠጡ ነበር፡፡ እንደዚሁም ቁመው ከመጠጣት ገስጸዋል (አስጠንቅቀዋል)፡፡ ይሁንና መቀመጥን የሚከለክል በቂ ምክንያት ሲኖር ቁመው መጠጣትን በይቅርታ አልፈውታል፡፡
- ከጠጡ በኋላ በቀኛቸው በኩል ለሚገኙ ባልደረቦቻቸው መጠጣቸውን ያጋሩ ነበር፤ የቱንም ያህል በዕድሜ የገፉት ከግራቸው በኩል ቢቀመጡም፡፡

## ጋብቻና የትዳር ሕይወታቸው

- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከዚህች ዓለማችሁ ውስጥ ሴቶችና ሽቶ እኔ ዘንድ ተወዳጅ ተደርገዋል፡፡ የዓይን ማረፊያዬም በሶላት ውስጥ ተደርጎልኛል፡፡»
- አዳራቸውን (ሌሊቶቻቸውን)፣ ቀረቤታቸውን (ጉድኝታቸውን) እና ቀለብን በሚስቶቻቸው መካከል (በፍትሐዊነት) ያከፋፍሉ ነበር፡፡
- እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጉዞ ለማድረግ ሲያቅዱ በሚስቶቻቸው መካከል ዕጣን ይጥሉ ነበር፡፡ ከዚያም በዕጣ የተመረጠችዋን ከራሳቸው ጋር ይዟት ይሄዱ ነበር፤ እንደዚሁም ለተቀሩት ሚስቶቻቸው (በጉዞ ወቅት ከአንዷ ጋር ብቻ በመሆናቸው ሲመለሱ የተቀሩትን ሴቶች የሌሊቶቻቸውን) ቀዷ አያወጡም ነበር፡፡»
- ከሚስቶቻቸው ጋር የነበራቸው የሕይወት ታሪክ ባማረ አብሮነት (አብሮ መኗኗር) እና ባማረ ምግባር ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡
- ከአንሷር የሆኑ ልጃ ገረዶችን ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጋር አብረው ይጫወቱ ዘንድ ወደርሷ ይልኩ ነበር፡፡ እርሷም በትርፍ ጊዜዋ አንዳችም ክልከላ የሌለበትን ነገር መሥራት በምትፈልግበት ጊዜ በዚያ (ሥራዋ) ላይ ይከተሏት (አብሯት ይሠሩ) ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በዓኢሻ ታፋ ላይ ተጋድመው በመቀመጥ ቁርአንን ይቀሩ ነበር፡፡ እርሷ በወር አበባዋ ዑደት ላይ ብትሆን እንኳን (ይህንኑ ያደርጉ ነበር)፡፡
- እርሷ በወር አበባዋ ዑደት ላይ በምትሆንበት ጊዜ አጭር ልብስን እንድትለብስ ያዟትና ከዚያም አንዳቸውም በአንዳቸው ይደሰቱ ነበር፡፡
- ፆም ላይ እያሉም ይስሟት ነበር፡፡
- ይህም ከሚስቶቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ከእዝነተ ረቂቅነታቸውና ከምግባራቸው ማማር ነው፡፡ ያም ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጨዋታን እንድትጫወት ሁኔታዎችን ያመቻቹላት ነበር፡፡ በጉዞ ላይ እያሉ ሁለት ጊዜ በሩጫ ተሽቀዳድመዋል፡፡ አንድ ጊዜም ሁለቱም ከቤታቸው (ለጉዞ) ሲወጡ ሰላማዊ ትግል ገጥመዋል፡፡
- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለጉዞ ሲወጡም ሆነ ከጉዞ ሲመለሱ በሌሊቱ ክ/ጊዜ ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው አያውቁም፡፡ ከዚህ ዓይነቱ (ልማድም) ይከለክሉ ነበር፡፡

## እንቅልፍንና ትኩረትን የሚመለከት መመሪያቸው

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለእንቅልፍ ወደ መኝታቸው በተጠጉ ጊዜ «ቢስሚከ አል-ሏሁም-መ አሕያ ወአሙት» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «አላህ ሆይ! እኔ የምኖረውና የምሞተውም ባንተ ስም ነው» ማለት ነው፡፡
- በሐዲሥ እንደተዘገበው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በየሌሊቱ ወደመኝታቸው በተጠጉ ቁጥር ሁለቱን መዳፎቻቸውን ያገናኙና (ከዚያም ውስጣቸውን ያጎደጉዱ)፣ ከዚያም በውስጣቸው እትፍ እትፍ ይሉና በውስጣቸውም ሱረቱል ኢኽላስን፣ ሱረቱል ፈለቅንና ሱረቱን ናስን ይቀሩበት ነበር፡፡ (ከዚያም) በሁለቱ መዳፎቻቸው አማካኝነት  ከራሳቸው፣ ከፊታቸውና ከፊት ለፊት የሰውነት ክፍሎቻቸው በመጀመር ከሰውነታቸው ክፍል የቻሉትን ሁሉ ያብሱበት ነበር፡፡ ይህንኑ (ተግባርም) ሦስት ጊዜ ይደጋግሙት ነበር፡፡
- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለእንቅልፋቸው ብለው መኝታቸው ላይ መጋደም በሚፈልጉበት ጊዜ ቀኝ እጃቸውን በጉንጫቸው ሥር ያደርጉና ከዚያም ሦስት ጊዜ «አል-ሏሁም-መ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተብዐሡ ዒባደከ» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «አላህ ሆይ! ባሮችህን ከሞት በምትቀሰቅስበት ዕለት ከቅጣትህ ጠብቀኝ» ማለት ነው፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜ «አል-ሐምዱ ሊሏሂል-ለዚ አሕያና በዕደ ማ አማተና ወኢለይሂን-ኑሹር» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «ለዚያ ከሞትን በኋላ ሕይወትን ለለገሰን አላህ ምስጋና ሁሉ ይገባው፤ መሰብሰቢያችንም ወደርሱ ነው» ማለት ነው፡፡ ከዚያም ሚስማክ በመጠቀም ጥርሳቸውን ይፍቁ/ይቦርሹ ነበር፡፡
- የሌሊቱን የመጀመሪያ ክፍል ይተኙና በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በሶላት ይቆሙ ነበር፡፡ (ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ) የሙስሊሞችን ጉዳዮች ለማስማመር ሲሉ የሌሊታቸው የመጀመሪያው ክፍል ወደመገባደድ ይቃረብ ነበር፡፡ (በሌላ አነጋገር ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ የተከታዮቻቸውን ጉዳዮች ለመከታተል ያመሹ ነበር)
- ዓይኖቻቸው ይተኙ ነበር፤ ይሁንና ልባቸው ንቁ እንደሆነ ያነጋ ነበር፡፡

## ሙዓመላን የሚመለከት መመሪያቸው

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች ጋር ይቃለዱና በቀልዳቸውም ውስጥ እውነትን ብቻ ይናገሩ ነበር፡፡
- የቃላት ጨዋታንም ይጫወቱ ነበር፤ ነገር ግን በቃላት ጨዋታቸው ውስጥ ከእውነት ውጭ ሌላ አይናገሩም ነበር፡፡
- (ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ መንገድንም ሆነ መፍትሔን) ራሳቸው ያመላክቱና አመላካችንም ይጠይቁ ነበር (ምክርንም ይሰጡ፤ ምክርንም ይጠይቁ ነበር)
- የታመመን ሰው ይጠይቁ፣ ጀናዛን ለመቅበር ይገኙ፣ ግብዣን ይቀበሉ፣ ጉዳዮቻቸውን ለመፈጸም ሲሉ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ሴቶች፣ ከምስኪኖችና ከአቅመ ደካሞች ጋር ይራመዱ ነበር፡፡
- እርሳቸውን የሚያወድስ ግጥምን ሰምተዋል፡፡ ለገጣሚውም ምንዳን ከፍለዋል (ሽልማትን ሰጥተውታል፤ ምንም እንኳን ከርሳቸው የላቁ መልካም ምግባራት ጋር ሲነፃፀር ግጥሙ አጭር የነበረ ቢሆንም)፡፡ ማንኛውም እርሳቸው የሚወደሱበት (ትክክለኛ ነገር) ከርሳቸው ተወዳሽነት አኳያ ሲታይ አነስተኛ የሆነ ክፍሉ ነው፡፡ ከርሳቸው ውጭ ላሉ ሰዎች የሚደረግ ውዳሴ ግን አብዛኛው ክፍሉ ውሸት ነው፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጫማቸውን በእጃቸው ጠግነዋል፡፡ ልብሳቸውንም በእጃቸው ሰፍተዋል፡፡ እንደዚሁም ባልዲያቸውን በእጃቸው ሰፍተዋል፡፡ ፍየላቸውን በእጃቸው አልበዋል፡፡ ልብሳቸውን አጣጥፈው አስቀምጠዋል፡፡ ቤተሰቦቻቸውንና ራሳቸውን አስተናግደዋል፡፡ በመስጊድ ግንባታ ላይ ከባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው የጭቃ ብሎኬቶችንም ተሸክመዋል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ከረሃብ የተነሳ ድንጋይን ሆዳቸው ላይ አስረዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጠግበው በልተዋል፡፡
- እንግዶቻቸውን አስተናግደዋል፤ በእንግድነትም ተስተናግደዋል፡፡
- በጭንቅላታቸው መሃል ላይ፣ ከእግራቸው ኋላ ላይ፣ አል-አኽደዐይን (በሁለቱም በኩል ከአንገት ኋላ ላይ የሚገኙ ሁለቱ የደም መልስ ቧንቧዎች) እና አል-ካሂል (በሁለቱ ትከሻዎች መካከል የሚገኝ ቦታና ወደ ጀርባም መግቢያ ነው) ላይ ታግመዋል (ሒጃማ ተደርገዋል)፡፡
- በመድኃኒት ታክመዋል፡፡ ሰዎችን በጋለ ብረት ተኩሰዋል፡፡ ግና እርሳቸው አልተተኮሱም፡፡ ሩቅያም አድርገዋል፡፡ ነገር ግን ለራሳቸው እንዲደረግላቸው ከሌሎች ጠይቀው አያውቁም፡፡ የታመመን ሰው (በአጠገቡ) የሚያስቸግር ነገር ከመፈጸም ከልክለዋል፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሙዓመላ ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ ናቸው፡፡ አንዳች ነገርን በተዋሱ ወይም በተበደሩ ጊዜም፣ ከተበደሩት ነገር በላይ አብዝተው ይመልሱ ነበር፡፡

## የአረማመዳቸው ሁኔታ

- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) የእግር መንገድ ሲሄዱ አረማመዳቸው ከሁሉም ሰው የፈጠነ ሲሆን ነገር ግን እርምጃቸው ከሁሉ ያማረና የተረጋጋ ነበር፡፡
- በአረማመዳቸው ከባልደረቦቻቸው የበለጠ ፈጣን ነበሩ፡፡ ስለሆነም እርሳቸው ላይ መድረስ በኃይለኛው ያታግላቸው ነበር፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ባዶ እግራቸውን አልያም በሽበጥ (ነጠላ) ጫማ አድርገው ይሄዱ ነበር፡፡
- ባልደረቦቻቸው ብዙውን ጊዜ ከርሳቸው ፊት ለፊት ይሄዱ ነበር፡፡ እርሳቸውም ከነርሱ ኋላ ይሆኑ ነበር፡፡
- በተናጠል ወይም በቡድን ሆነው ከባልደረቦቻቸው ጋር ይሄዱ ነበር፡፡

## አላህን የማውሳት ሁኔታቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኃያሉ አላህን በማውሳት (እና በማስታወስ) ረገድ ከሰዎች ሁሉ እጅግ የተሟሉት ናቸው፡፡ ይልቁንስ ንግግራቸው ሁሉ በአላህ ትውስታ ውስጥ (የተገደበ) እና ለርሱም የተደረገ ነው፡፡ ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜ አላህን ያውሱ ነበር፡፡ ሶላታቸውን በሚከፍቱበት ጊዜ፣ ከቤታቸው በሚወጡበት ጊዜም፣ መስጊድ በሚገቡበት ጊዜም፣ በጠዋትና በማታ ክ/ጊዜም፣ ልብሶቻቸውን በሚለብሱበት ጊዜም፣ ወደማረፊያ በሚገቡበት ወይም በሚወጡበት ጊዜም፣ መፀዳጃ ቤት በሚገቡበት ጊዜም፣ ዉዱእ ከማድረጋቸው በፊትና ካደረጉ በኋላም፣ የሶላት ጥሪን (አዛንን) በሚሰሙበት ጊዜም፣ አዲስ ጨረቃን በሚመለከቱበት ጊዜም፣ ከመመገባቸው በፊትና ከተመገቡ በኋላም፣ በሚያስነጥሳቸው ጊዜም፣ … ወዘተ አላህን ያወሱ ነበር፡፡

## የተፈጥሮ ሱነኖችና እነርሱንም መከተልን የሚመለከት መመሪያቸው

### የሱነኖች ብዛት

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አስር (ተግባራት) ከፊጥራ ተርታ የሚመደቡ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስን) ማሳጠር፣ ፂምን ማሳደግ፣ ሲዋክን (የጥርስ መፋቂያን) መጠቀም፣ አፍንጫን በውሃ ማፅዳት (አል-ኢስቲንሻቅ)፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ የጣት መገጣጠሚያዎችን መታጠብ፣ የብብት አካባቢ ፀጉርን መንጨት፣ የብልት አካባቢ ፀጉርን መላጨት፣ (ከሰገራ ወይም ከሽንት በኋላ) የግል አካላትን በውሃ ማፅዳት ናቸው፡፡ የሐዲሡ አስተላላፊ አስረኛውን ረስቶታል፡፡ (ለፊጣን መረጃ ሲባል 10ኛው ነጥብ ግርዛት ነው፡፡)»

### ከቀኝ መጀመር

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቀኝ የመጀመር ልማዳቸው የሚያስደንቅ ነው፡፡ ጫማቸውን በሚያደርጉበት፣ በሚራመዱበት፣ ንጽሕናቸውን በሚያሟሉበት፣ አንዳች ነገርን በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር፡፡ ቀኝ እጃቸውን ለመመገብ፣ ለመጠጣትና ለጠሃራ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ግራ እጃቸውን ደግሞ ለመፀዳዳትና ሌሎችንም ተመሳሳይ የሆኑ ቆሻሻ ነገሮችን ለማስወገጃነት ይጠቀሙበት ነበር፡፡

### ፀጉር

የራስ ፀጉርን በተመለከተ የነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) መመሪያቸው ወይ እንዳለ መተው አልያም እንዳለ መላጨት ነበር፡፡

### ሲዋክ

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሲዋክ መጠቀምን ይወዱ ነበር፡፡ በሚፆሙበትና በማይፆሙበት ጊዜም ሲዋክን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜም፣ ዉዱእን በሚያደርጉበት ጊዜም፣ ከሶላት በፊትም (ወደ ሶላት ሊገቡ በቆሙበት ጊዜ) እና ወደ ቤት በሚገቡበት ጊዜም ሲዋክን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ጥርሳቸውን ሲፍቁ የነበረው ዑዱል አራክ ከሚባል የዛፍ ዓይነት በሚገኘው መፋቂያ ነበር፡፡

### ሽቶ

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሽቶ መጠቀምን ያበዙ ነበር፡፡ እንደዚሁም ሽቶን ይወዱ ነበር፡፡

### ፂምና ቀድሞ ቀመስ

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «አጋሪያን (ከሚያደርጉት) ተቃራኒ ሁኑ፡፡ ስለሆነም ፂምንም አሳድጉ፤ የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስንም) በአጭሩ ቁረጡ፡፡»

### የጊዜ ገደብ

አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስን) ማሳጠር፣ ጥፍርን መቁረጥና (የብልት አካባቢ ፀጉርን መላጨትን) በተመለከተ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጊዜ ገደብ አስቀምጠውልናል፡፡ ይህም ከአርባ ቀናትና ሌሊቶች በላይ (ባሉበት) እንዳንተዋቸው ነው፡፡»

## ንግግራቸው

- እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ልክ እናንተ አሁን እንደምታደርጉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፍጥነት በተሞላበት አኳኋን አይናገሩም ነበር፤ ይልቁንስ እነዚያ በዙሪያቸው የተቀመጡ ሰዎች በቃላቸው መሸምደድ በሚያችስላቸው መልኩ በተብራራና አለያይ በሆነ ንግግር ይናገሩ ነበር፡፡»
- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) አብዛኛውን ጊዜ ንግግራቸውን ሦስቴ የሚደጋግሙበት ምክንያት ሰዎች በቀላሉ እንዲረዱላቸው ነበር፡፡ ሰላምታን በሚያቀርቡበት ጊዜም ሦስት ጊዜ ደጋግመው ያቀርቡ ነበር፡፡
- አስፈላጊ ባልሆነበት ጊዜ አይናገሩም ነበር፡፡ ሆኖም ግን በተናገሩ ጊዜ እጥር ምጥን አድርገው በጠቅላይ ቃላት ይናገሩ ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለማይመለከታቸው ጉዳይ ፈፅሞ ተናግረው አያውቁም፡፡ እንደዚሁም ምንዳ ማግኘትን በሚከጅሉበት ጉዳይ ዙሪያ ቢሆን እንጂ አይናገሩም ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለጌም ሆነው አያውቁም፡፡ የብልግና ቃላትንም ተናግረው አያውቁም፡፡ ጮኽ ብለውም ተናግረው አያውቁም፡፡

**የንግግራቸው፣ የሳቃቸው፣ የለቀወሷቸውና የኹጥባቸው ሁኔታ**

**ሳቃ-ቸው**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሳቃቸው ሁሉ የፈገግታ ነበር፡፡ እርሳቸው ሲበዛ የሳቁበት ሁኔታ ቢኖር የመንጋጋ ጥርሶቻቸው መታየት የቻሉበት (ኢጋጣሚ) ላይ ነበር፡፡

**ለቅሷቸው**

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁከትን በሚፈጥር ሁኔታ ከፍ ባለ ድምጽ አልቅሰው አያውቁም፡፡ ነገር ግን በኃይለኛው ያነቡና ከደረታቸውም የመንሰቅሰቅ ድምጽ ይሰማ ነበር፡፡
- አንዳንድ ጊዜ የለቅሷቸው ምክንያት ለሟች ካላቸው እዝነት የተነሳ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜም የለቅሷቸው ምክንያት ለተከታዮቻቸው ካላቸው ፍርሃት ወይም የሌላውን ስሜት ከመጋራት ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ የለቅሱ ነበር፡፡ አንዳንድ ገ ዜም ቁርአንን ሰ ሰሙ የለቅሱ ነበር፡፡

**ኹጥባቸው**

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሬት ላይ ቁመውም፣ ሚንበር ላይ ወጥተውም፣ በወንድ ግመል ላይ ሆነው እየተጓጓዙም፣ በሴት ግመል ላይ ሆነው እየተጓጓዙም ኹጥባ አድርገዋል (ምክርን ለግሰዋል)፡፡
- ጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባ በሚያደርጉበት (ሕዝቡን በሚመክሩበት ጊዜ) ዓይኖቻቸው ይቀሉ፣ ድምፃቸው ይጎላ፣ ቁጣቸውም ይበረታ ነበር፤ (ይህም) ልክ እንደዚያ የጦር ሠራዊት አስጠንቃቂ እስከሚመስሉ ድረስ ነበር፡፡»
- ኃያሉ አላህን በማመስገን (በማወደስ) የከፈቱት ቢሆን እንጂ አንድም ኹጥባ አድርገው አያውቁም፡፡
- የተመካሪዎችን ጉዳይ በሚፈጽምና ለእምርታቸው (አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጉዳይ ዙሪያ) በማንኛውም ወቅት ኹጥባን ያደርጉ ነበር፡፡

# ሁለተኛው ፈተና

| ውሸት | እውነት | ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| □ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልብሳቸውን ሲለብሱ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር፡፡ |
| □ | £ | አብዛኛውን ምግባቸው የሚመገቡት መሬት ላይ በሱፍራ ተደርጎ ነበር፡፡ |
| □ | £ | ነብዩ (ሰ.ወ) ለጉዞ ሲወጡም ሆነ ሲገቡ በሌሊት ወደ ቤተሰቦቻቸው አይገቡም ነበር፤ ይህንኑ ማድረግንም ይከለክሉ ነበር፡፡ |
| □ | £ | ከረሃብ መጥናት የተነሳ ሆዳቸው ላይ ድንጋይን አስረዋል፡፡ |
| □ | £ | ለሌሎች ሩቃ አድርገዋል፡፡ እንዲደረግላቸው ግን አልጠየቁም፡፡ |
| □ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወስዋስ ሰዎች የተፈተኑባቸውን ተግባራት ፈፅሞ አልተገበሩም፡፡ ከወስዋስ ሰዎች ቢድዓም (ከየት-መጤ ተግባራትም) ከልክለዋል፡፡ |
| □ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በትክክለኛው የሐነፊያ እምነት የተላኩ ሲሆን፣ እርሱም የሺርክ እና ሐላልንም ሐራም የማድረግ ልማዶች ተቃራኒ ነው፡፡ |
| □ | £ | ልጆቻቸው ሰባት ሲሆኑ፣ ከነርሱም አራቱ ወንዶችና ሦስቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ |
| □ | £ | ሁሉም ልጆቻቸው ከኸዲጃ (ረ.ዐ) የተወለዱ ሲሆኑ ሌሎች ግን ምንም አልወለዱም፡፡ |
| □ | £ | ሁሉም ልጆቻቸው የሞቱት ከርሳቸው በፊት ነበር፡፡ |
| □ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘጠኝ ሚስቶቻቸውን ትተው እንደሞቱ በዑለሞች መካከል ምንም አለመግባባት የለም፡፡ እነርሱም፡- ዓኢሻ፣ ሐፍሳ፣ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ፣ ኡም-ሙ ሰለማ፣ ሰፊይ-ያ፣ ኡም-ሙ ሐቢባ፣ መይሙና፣ ሰውዳና ጁወይሪያ (ረ.ዐ) ናቸው፡፡ |
| □ | £ | ኃያሉ አላህ በጂብሪል በኩል ለኸዲጃ (ረ.ዐ) ሰላምታን ልኮላታል፡፡ ይህም ለርሷ ለየት ባለ ሁኔታ የተሰጠ ትሩፋት ሲሆን ለሌላ ሴት ግን አይታወቅም፡፡ |

1. የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተወዳጁ ቀለም፡- ሀ/ ነጭ ለ/ ጥቁር ሐ/ ከቀለማት የገራላቸውን ሁሉ
2. ልብሳቸው፡- ሀ/ የሱፍ ልብስን አይለብሱም ነበር ለ/ የጥጥና የላይነን ልብሶችን ይለብሱ ነበር ሐ/ ያላቸውን የትኛውንም ዓይነት ልብስ ይለብሱ ነበር መ/ ሀ እና ለ
3. ልብሳቸው፡- ሀ/ ከልብሶች ሁሉ እጅግ ውዱ ነበር ለ/ ከዛሂድነት መገለጫ ልብሶች በላይ ያረጀ ያፈጀ ነበር ሐ/ በሁለቱ መሀከል መካከለኛ የሆነ ነበር

1. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቢስሚ-ሏህ እና አል-ሐምዱ ሊ-ሏህ ሲሉ የነበረው፡- ሀ/ በምግባቸው መጀመሪያ ላይ ለ/ በመጨረሻው ላይ ሐ/ በመጀመሪያም በመጨረሻም ላይ
2. አብዛኛውን ጊዜ ሲሰጡ የነበረው፡- ሀ/ ተቀምጠው ለ/ ቁመው ሐ/ ሁለቱም
3. «ከዚህች ዓለማችሁ እኔ ዘንድ ..... ተወዳጅ ተደርገዋል» ብለዋል፡- ሀ/ ሴቶች ለ/ ሽቶ ሐ/ ሁለቱም
4. «የዓይኖቼ ማረፊያ ..... ውስጥ ተደርጎልኛል» ብለዋል፡- ሀ/ በጀነት ለ/ በሶላት ሐ/ ሁለቱም
5. ከሚስቶቻቸው ጋር የነበራቸው ታሪክ ጥሩ የነበረው፡- ሀ/ በአኗኗር ለ/ በምግባር ሐ/ ሁለቱም
6. አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዳወሩት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቀድሞ ቀመስ በማሳጠር፣ ጥፍርን በመቁረጥ (የብልት አካባቢ ፀጉርን በመላጨት) ረገድ ከ ....... በላይ እንዳንተዋቸው የጊዜ ገደብን አስቀምጦልናል፡፡ ሀ/ 30 ቀናት ለ/ 40 ቀናት ሐ/ 50 ቀናት
7. የራስ ፀጉርን በተመለከተ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ፡- ሀ/ ከፊሉን ይላጩና ከፊሉንም ይተውት ነበር ለ/ እንዳለ ይተውት አልያም እንዳለ ይላጩት ነበር
8. ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲዋከን ይወዱና በ .......................... ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ሀ/ በሚፆሙበት ጊዜ ለ/ በማይፆሙበት ጊዜ ሐ/ ሁለቱም
9. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሳቃቸው፡- ሀ/ ሁሉም ፈገግታ ነበር ለ/ አብዛኛው ፈገግታ ነበር
10. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላኩት፡- ሀ/ ወደ መላው የሰው ዘር ለ/ ወደ ጋኔኖችና የሰው ልጆች
11. የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምርጧ ሴት ልጅ፡- ሀ/ ሁላቸውም ለ/ ፋጢማ ሐ/ ዘይነብ
12. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በ ......... ታፋ ላይ ተጋድመው ተቀምጠው እንጂ በሌላዋ ላይ (በዚህ ሁኔታ) መለኮታዊ ራዕይ ወርዶባቸው አያውቅም ነበር፡፡ ሀ/ በዓኢሻ ለ/ ሐፍሳ ሐ/ ኡም-ሙ ሰለማ

| የታመመን | ከጋላሞታዎች፣ ድሆችና ደካሞች | ግብዣን | ቀብር ላይ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- |
|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | ☐ | ይጠይቁ ነበር |
| £ | £ | £ | ☐ | ይገኙ ነበር |
| £ | £ | £ | ☐ | ይቀበሉ ነበር |
| £ | £ | £ | ☐ | ጋር አብረው ይራመዱ ነበር |

| ቤተሰባቸውን ራሳቸውን | ጫማቸውን በእጆቻቸው | ልብሳቸውን በእጆቻቸው | መስጊድ ለመስራት ብሎኬቶችን | ፍየላቸውን | ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባራት መካከል፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | ☐ | ይጠግኑ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | ☐ | ይሰፉ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | ☐ | ያልቡ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | ☐ | ያስተናግዱ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | ☐ | ይሸከሙ ነበር |

| ቀድሞ ቀመስ | ፂም | የብልት ፀጉር | የብብት | ጥፍር | ከሱነን ተግባራት መካከል፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | መከርከም |
| £ | £ | £ | £ | £ | ማስረዘም |
| £ | £ | £ | £ | £ | መቁረጥ |
| £ | £ | £ | £ | £ | መንጨት |
| £ | £ | £ | £ | £ | መላጨት |

| ያለውን ምግብ | ሐራም ሳያደርጉ ይተውት ነበር | የተመገቡት ቢሆን እንጂ | በሌለ ምግብ | የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአመጋገብ ሁኔታ፡- |
|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | □ | እምቢኝ ብለው አይመልሱም ነበር |
| £ | £ | £ | □ | ጫና አይፈጥሩም ነበር |
| £ | £ | £ | □ | ከንጹሕ ነገሮች የቀረበላቸውን |
| £ | £ | £ | □ | ውስጣቸው ያልፈለገው ሲሆን |

| ሦስት | በአምስት ጣቶች | በአንድ ጣቱ | ምግብ | በጨረሱ ጊዜ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | የሚመገቡበት ጣቶች ብዛት |
| £ | £ | £ | £ | £ | ጣቶቻቸውን ይልሷቸው ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | በላይ ይበልጥ የተከበሩ ናቸው |
| £ | £ | £ | £ | £ | ኩራተኛ ሰው የሚመገበው |
| £ | £ | £ | £ | £ | ሆዳም ሰው የሚመገበው |

## ልዩ መገለጫዎቻቸው

### ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልዩ መገለጫዎች መካከል

| | |
|---|---|
| በቀጥተኛና ንጹሕ ሃይማኖት ተልከዋል | ኢማም ኢብኑል ቀይም (ረሂመሁሏህ) እንዲህ ብለዋል፡- «የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተልዕኮ ቀጥተኛና ንጹሕ (ሃይማኖትን) አንድ ላይ ያሰባሰበ ሲሆን፣ እርሱም በተውሒድ ረገድ ቀጥተኛ ነው፡፡ በአኽላቅ ረገድ ደግሞ ንጹሕ ነው፡፡ የሁለቱ ጉዳዮች ተቃራኒያቸው ደግሞ ሺርክ (በአላህ ማጋራት) እና ሐላል የሆነን ነገር ሐራም ማድረግ ናቸው፡፡» |
| ወደጋኔንና የሰው ዘር ሁሉ ተልከዋል | ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከኔ በፊት ያለፈ) ነብይ ሁሉ ወደራሱ ሕዝቦች (ወገኖች) ብቻ ይላክ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔ የተላኩት ወደ መላው የሰው ዘር ነው፡፡» |
| የተሰጣቸው መጽሐፍና ጥሪያቸው | ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርኣን) በጌታቸው ፈቃድ ሰዎችን ከጨለማዎች ወደ ብርሃን፣ አሸናፊ ምስጉን ወደሆነው ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው፡፡» (ሱረቱ ኢብራሂም 14፡1)* |
| የተሰጧቸው ተአምራት | ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተሰጧቸው ተአምራት መካከል እጅግ የላቀው ክቡር ቁርኣኑ ነው፡፡ እንደዚሁም ለርሳቸው ከዚያ ላይ ድርሻ ቢኖራቸው እንጂ ከርሳቸው በፊት ያለፈ ነብይም ሆነ መልዕክተኛ ከተአምር አንድንም አልተሰጠም፡፡ |
| ጠይአቸውን የሚመለከት ድንጋጌ | ታላቅ የክህደት ወንጀልን የፈጸመ ከሀዲ ይሆናል፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«ጠይህ (የሚጠላህ) እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው፡፡» (ሱረቱ አል-ከውሠር 108፡3)* |
| እርሳቸውን መውደድ የኢማን አካል መሆኑ | የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ እርሱ ዘንድ ከልጁ፣ ከአባቱና ከመላው የሰው ዘር ሁሉ ይበልጥ ተወዳጅ እስከምሆን ድረስ ከናንተ መካከል አንዳችሁም አላመነም፡፡» |
| የአላህ ወዳጅ መሆናቸው | የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእውነቱ አላህ እኔን ወዳጁ አድርጎ ይዞኛል፤ ልክ እርሱ ኢብራሂምን ወዳጁ አድርጎ እንደያዘው ሁሉ፡፡» |
| የቁራጥነት ባለቤት ከሆኑ ነብያት መካከል አንዱ መሆናቸው | ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም፣ ከኑሕም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም፣ ከመርየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ከነርሱም የከበደን ቃል ኪዳን ያዝን፡፡» (አል-አሕዛብ 33፡7)* |
| ዕውቀታቸው | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «እኔ ከናንተ መካከል አላህን ይበልጥ አዋቂው ነኝ» ብለዋል፡፡ አላህ እንዲህ ብለዋል፡- *«ለእናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም፡፡ ሩቅንም አላውቅም፡፡ ለናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም፡፡ ወደእኔ የሚወርደልኝን እንጂ ሌላን አልከተልም ...› በላቸው፡፡» (አል-አንዓም 6፡50)* |

## ከሌዩ መገለጫዎቻቸው

### ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) የታዘዙና ያመፁ ሰዎችን የሚመለከት ድንጋጌ

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል:- *«በላቸው:- ‹አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና። ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና።› … » (ኣሉ ዒምራን 3፡31)*

*«እናንተም የበላዮች ስትኾኑ ምእመናን እንደኾናችሁ አትስነፉ፤ አትዘኑም።» (ኣሉ ዒምራን 3፡139)*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «እምቢ ያለኝ ሰው ሲቀር ሁላችሁም ጀነት ትገባላችሁ» አሉ። እነርሱም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እምቢ ባዩ (የሚያምፀው) ማነው?» አሉ። እርሳቸውም «እርሱ ያ እኔን ታዘዘ ሰው ጀነት ገባ።እኔን የሚያምጽ ሁሉ ግን እርሱ ያ (ጀነት ለመግባት) እምቢ ያለ ነው» አሉ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዚህም ብለዋል:- «የኔን ትዕዛዝ በሚቃረን ሰው ላይ ውርደትና አናሳነት ተደርጎበታል።»

### ተከታዮቻቸው

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል:- *«ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ፤ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ። … » (ኣሉ ዒምራን 3፡110)*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «በዚያ ነፍሴ በእጁ በሆነችው (ጌታዬ) እምላለሁ! እናንተ የጀነት ነዋሪዎችን ግማሹን እንደምትሆኑ ተስፋ አድርጋለሁ።»

### ከተማቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የትውልድ ሀገራቸው መካ ነው። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል:-

*«ለሰዎች (መጸለያ) መጀመሪያ የተኖረው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመሪያ ሲኾን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ነው። በውስጡ ግልጽ የኾኑ ተዓምራት የኢብራሂምም መቆሚያ አልለ። ወደ ውስጡ የገባ ሰው ጸጥተኛ ይኾናል። ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።» (ኣሉ ዒምራን 3፡96-97)*

ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት መካ ቅድስት ቦታ ናት። እንዲህም ብለዋል:- «በእውነቱ አላህ ሰማያትንና ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ይህቺን ከተማ የተቀደሰች አድርጓታል። ስለሆነም እርሷ በአላህ ውሳኔ መሠረት (እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ) ቅድስት ናት።» ከዚህም በተጨማሪ ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት እስከ ዕለተ ትንሳኤው ድረስ መካ የሙስሊሞች ናት። እንዲህም ብለዋል:- «ከመካ መከፈት በኋላ ስደት የለም።»

### ቂብላቸው

የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የሶላት አቅጣጫቸው (ቂብላቸው) ከዕባ ነው። ይሁንና መጀመሪያ ላይ ወደቤይተል መቅዲስ ነበር። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል:-

*«የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን። ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር። የትም ስፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ። … » (አል-በቀራ 2፡144)*

እንደዚሁም መካ ውስጥ የሚገኘው መስጂድ አል-ሐራም በምድር ላይ የተኖረው የመጀመሪያው መስጂድ ነው። አቡ ዘር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል:- «እኔ የአላህ መልዕክተኛን በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተኖረው መስጂድ ጠየቅኳቸው። እርሳቸውም ‹መስጂድ አል-ሐራም ነው› አሉኝ።»

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- «እርሱ ያ (የሐጅ ሥነ-ሥርዓትን በመፈጸም ሐሳብ) ወደዚህ ቤት (መስጂድ) የመጣ ሰው፣ ፀያፍ ነገርን ያልተናገረና የአመፅ ተግባርንም ያልፈጸመ ሰው፣ ልክ እናቱ እንደወለደችው ዕለት (ከኃጢአቱ ነፃ ሆኖ) ይመለሳል።»

| ከልዩ መገለጫዎቻቸው | ቂብላቸው | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህም ብለዋል፡- «በመስጂድ አል-ሐራም ውስጥ የሚሰገድ (አንድ) ሶላት ከአንድ መቶ ሺ ሶላቶች ጋር እኩል ሲሆን በኔ መስጂድ ውስጥ የሚሰገድ አንድ ሶላት ደግሞ ከአንድ ሺ ሶላቶች ጋር እኩል ነው፤ በበይተል መቅዲስ የሚሰገደው አንድ ሶላት ደግሞ ከአምስት መቶ ሶላቶች ጋር እኩል ነው፡፡»<br>ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህም ብለዋል፡- «ወደሦስት መስጂዶች ካልሆነ በስተቀር ወደማንኛውም ቦታ (ሃይማኖታዊ) ጉዞ አይደረግም፡፡ እነዚህም መስጂዲል ሐራም (መካ)፣ የኔ መስጂድ (መስጂድ አን-ነበዊ - መዲና) እና መስጂድ አል-አቅሷ (ኢየሩሳሌም) ናቸው፡፡»<br>ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዚህም ብለዋል፡- «ለመፀዳዳት በምትሄዱበት ጊዜ፣ በፊታችሁ ወደቂብላ አትዙሩ፤ ጀርባችሁንም ወደርሱ አታዙሩ፡፡ ይልቁንስ ወይ ወደ ምሥራቅ አልያም ወደ ምዕራብ ዙሩ፡፡» |
|---|---|---|

## ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው

### ሰባቱ ልጆቻቸው - 3 ወንዶች እና 4 ሴቶች

| | |
|---|---|
| [1] አል-ቃሲም - ይህ የርሳቸው ቅፅል ስም ጭምር ነው:: | [2] ዘይነብ (ረ.ዐ) |
| [3] ሩቀይ-ያ (ረ.ዐ) | [4] ኡም-ሙ ኩልሡም (ረ.ዐ) |
| [5] ፋጡማ (ረ.ዐ) | [6] ዐብዱሏህ - ሌላ ስሙ አጥ-ጠይ-ዪብ እና አጥ-ጣሂር ነው |

[7] ኢብራሂም፣ እርሱ የማሪያቱ አል-ቂብጢይ-ያ ልጅ ሲሆን እርሷ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድብቅ ሚስት ነበረች:: ከኢብራሂም በስተቀር የተቀሩት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች ሁሉ ከኸዲጃ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) የተወለዱ ናቸው:: ከርሷ ውጭ ሌሎች ሚስቶቻቸው ለርሳቸው ምንም ልጅ አልወለዱላቸውም::

ልጃቸው ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ስትቀር ሁሉም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች ከርሳቸው በፊት የሞቱ ናቸው:: እርሷም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕልፈት በኋላ ስድስት ወራት ቆየች:: በትዕግስቷና ከአላህ ዘንድ (ምንዳን አገኛለሁ) ብላ በመተሳሰቧ ሳቢያ ኃያሉ አላህ በዓለማት ሴቶች ላይ ብልጫን በምታገኝባቸው ደረጃዎች ከፍ አደረጋት:: በደፈናው ሲታይ ከሴት ልጆቻቸው ሁሉ በላጭዋ ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ናት:: ሁሉም ሴት ልጆቻቸውም የእስልምና ፀጋ ላይ ደርሰዋል:: እስልምናንም ተቀብለዋል:: ከርሳቸውም ጋር ወደ መዲና ተሰደዋል::

### በአባታቸው በኩል ያሉ ፲፩ አጎቶቻቸው

1. ሀምዛ (ረ.ዐ) - የሰማዕታት አለቃ
2. አል-ዐብ-ባስ (ረ.ዐ)
3. ዐቡ ጧሊብ፣ ዐብዱ መናፍ
4. አቡ ለሀብ፣ ዐብዱል ዑዝ-ዛ
5. ዙበይር
6. ዐብዱል ከዕባ
7. አል-ሙቀዊም
8. ዲራር
9. ቁሠም
10. አል-ሙጊራ - ሌላ ስማቸው ሐጀል
11. አል-ገይዳቅ፣ ስማቸው ሙስዐብ ነው

በአባታቸው በኩል ከሚዛመዷቸው አጎቶቻቸው መካከል ሀምዛ እና አል-ዐብ-ባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) ሲቀሩ የተቀሩት አንዳቸውም እስልምናን አልተቀበሉም::

| በአባታቸው በኩል ያሉ 6ቱ አክስቶቻቸው | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሰፍ-ፊያ - የአዝ-ዙበይር ኡብን ዐው-ዋም (ረ.ዐ) እናት | 2. ኡሙ ሐኪሚን አል-በይዳእ | | | |
| 3. ዓቲካ | 4.በር-ራ | 5. ኡርዋ | 6. ኡመይማ | |

| ﷺ የሚስቶቻቸው ስሞች- የመጀመሪያ ፊደል በማገናኘት | |
|---|---|
| حجز | አል-ሓኡ:- ሐፍሳ ቢንት ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አል-ጂም:- ጁወይሪይ-ያ ቢንት አል-ሓሪሥ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አዝ-ዛይ:- ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ እና ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) |
| صخر | አስ-ሷድ:- ሰፊይ-ያ ቢንት ሑየይ-ዩ ኢብን አኽጠብ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አል-ኻኡ:- ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አር-ራኡ:- ኡም-ሙ ሐቢባ ረምላ ቢንት አቢ ሱፍያን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) |
| سمعه | አስ-ሲን:- ሰውዳ ቢንት ዘምዓ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አል-ሚም:- መይሙና ቢንት አል-ሓሪሥ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አል-ዐይን:- ዓኢሻ ቢንት አቢ በክር (ረዲየሏሁ ዐንሃ)<br>አል-ሃ:- ኡም-ሙ ሰለማ ሂንድ ቢንት አቢ ኡመይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) |

**ኸዲጃ (ረ.ዐ)**

ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል የመጀመሪያዋ ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ አል-ቁረሺይ-ያ አል-አሰዲይ-ያ (ረ.ዐ) ስትሆን እርሷንም ያገቧት በነብይነት ከመላካቸው በፊት ነበር፡፡ ሲጋቡም ዕድሜዋ 40 ዓመት ነበር፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷ በሕይወት እስካለች ድረስም ሌላ ሚስትን አላገቡም ነበር፡፡ ኢብራሂም ሲቀር ሁሉም ልጆቻቸውም ከኸዲጃ የተወለዱ ናቸው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የነብይነት ማዕረጋቸውን እንደተቀበሉ ኸዲጃ ከጎናቸው ሆና ታበረታታቸውና ከርሳቸውም ጋር ትታገል ነበር፡፡ በሕይወቷና በገንዘቧ አማካኝነት ኃይል ትሆናቸው ነበር፡፡ ስለሆነም አላህ በመላኢካው ጂብሪል በኩል ለኸዲጃ ሰላምታን ላከላት፡፡ ይህም ለርሷ ብቻ የተለየና ከርሷ ውጭ ላሉ ሴቶች ሁሉ ተሰጥቶ የማይታወቅ ትሩፋት ነው፡፡ እርሷም ከኢስላማዊ ስደት በፊት በሦስት ዓመታት አስቀድማ ሞተች፡፡

**ሰውዳ (ረ.ዐ)**

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከኸዲጃ ሕልፈት አጭር ቆይታ በኋላ ሰውዳ ቢንት ዘምዓ አል-ቁረሺይ-ያን አገቡ፡፡ እርሷም (የኋላ ኋላ) ሌሊቶቿን በስጦታ መልክ ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ያበረከተች ናት፡፡

**ዓኢሻ (ረ.ዐ)**

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዓኢሻ አስ-ሲድ-ዲቃ ቢንት አስ-ሲድ-ዲቅን አገቧት፡፡ ዓኢሻ (ረ.ዐ) የቅፅል ስሟ ኡም-ሙ ዐብዱሏህ ነው፡፡ ዓኢሻ ያቺ ኃያሉ አላህ ከሰባት ሰማያት በላይ ሆኖ ከተወራባት ቅጥፈት ነፃ ያደረጋት ሚስታቸው ናት፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድም ከሁሉም በላይ ይበልጥ ተወዳጅ ናት፡፡ ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ከመጋባቷ በፊት ለርሳቸው ከሐር በሆነ ቁራጭ ልብስ ውስጥ ሆና የቀረበችላቸው በመላኢካ አማካኝነት በሕልማቸው ውስጥ ነበር፡፡ መላኢካውም «ይህቺ ሚስትህ ናት» አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዓኢሻን በሸው-ዋል ወር ውስጥ፣ እርሷ የስድስት ዓመት ልጅ ሆና ሳለች ኒካሕ አሰሩላት፡፡ ከዚያም ዕድሜዋ 9 ዓመት በሞላ ጊዜ በአንደኛው የሂጅሪያ ዓመት በጋብቻ ጠቅልለው ወሰዷት፡፡ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከርሷ ውጭ ልጃ ገረድ አግብተው አያውቁም፡፡ እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በታፋዋ ላይ ተጋድመው ተቀምጠው ሳሉ እንጂ በሌላዋ ላይ ሳሉ መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) አልወረደባቸውም፡፡

ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከፍጡራን መካከል መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅዋ ናት፡፡ የርሷ ንጹሕነትም ከሰማያት በላይ የወረደ ሲሆን በርሷ ላይ የውሸት ወሬን የቀጠፈ ግለሰብም ከሀዲ መሆኑን ኡም-ማው በአንድ ድምጽ ተስማምተውበታል፡፡ ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ሁሉ ዲኑን ይበልጥ የተገነዘበችና ከሁላቸውም በላይ ዐዋቂ ናት፡፡ በደፈናው ከኡምማው ሴቶች ሁሉ ይበልጥ ፊቂሃ እና ዓሊማ ናት፡፡ ታላላቆቹ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሳይቀሩ አስተያየቷን ይሹና ሃይማኖታዊ ብያኔዋንም ይጠይቁ ነበር፡፡

**ሐፍሳ (ረ.ዐ)**

በማስከተልም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሐፍሳ ቢንት ዑመር ኢብን አል-ኸጧብን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) አገቧት፡፡ እርሷ አስቀድማ ከመጀመሪያ ባሏ ከኹነይስ ኢብን ሑዛፋ አስ-ሰሀሚይ-ይ ጋር እስልምናን ተቀብላ ነበር፡፡ ከርሱም ጋር ወደ መዲና ተሰድዳ ነበር፡፡ እርሱም ከኡሑድ ዘመቻ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞተ፡፡ ስለሆነም ከዚያ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አገቧት፡፡

**ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ (ረ.ዐ)**

በማስከተልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ ኢብን አል-ሓሪሥ አል-ቀይሲይ-ያን፣ ከበኑ ሂላል ኢብን ዓሚር ጎሳ አገቧት፡፡ ይሁንና እርሷ መልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ካገባች ከሁለት ወራት በኋላ ሞተች፡፡ እርሷ የምስኪኖች እናት የሚል ሌላ ስምም ተሰጥቷት የነበረች ናት፡፡

**ኡም-ሙ ሰለማ (ረ.ዐ)**

በማስከተልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡም-ሙ ሰለማ ሂንድ ቢንት አቢ ኡመይ-ያ አል-ቁረሺይ-ያ አል-መኽዙሚይ-ያን አገቧት፡፡ የአቡ ኡመይ-ያ ስማቸው ሑዘይፋ ኢብን ሙጊራ ነው፡፡ ኡም-ሙ ሰለማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል መጨረሻ ላይ የሞተች ናት፡፡ የሞተችውም ከሂጅሪያ በኋላ በ62 ዓመት ነበር፡፡

**ጁወይሪያ (ረ.ዐ)**

በተመሳሳይ መልኩ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጁወይሪይ-ያ ኢብን አል-ሓሪሥ ኢብን አቢ ዲራር አል-ሙስጠሊቂይ-ያን አግብተዋል፡፡ እርሷ ከበኒ አል-ሙስጠሊቅ ምርኮኞች መካከል ነበረች፡፡ ነፃነቷን ለማግኘት ስትልም የመልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) እገዛ ፍለጋ ወደርሳቸው መጣች፡፡ ስለሆነም እርሳቸውም ይህንኑ መለሱላትና አገቧት፡፡

**ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ (ረ.ዐ)**

በማስከተልም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ጀሕሽን ከበኑ አሰድ ኢብን ኹዘይማ ጎሳ አገቧት፡፡ እርሷም በአባታቸው በኩል የምትዛመዳቸው የአክስታቸው ኡመይማ ልጅ ናት፡፡ ቀጣዩ የአላህ ቃልም የወረደው እርሷን አስመልክቶ ነው፡- *«... ዘይድም ከእርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ አጋባንህ፡፡ ... » (አል-አሕዛብ 33፡37)*

በዚህም ሳቢያ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ በተቀሩት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ላይ እንዲህ እያለች ትፎክር ነበር፡- «እናንተን (ለአላህ መልዕክተኛ) የዳሩዋችሁ ቤተሰቦቻችሁ ናቸው፡፡ ይሁንና (እኔን ለአላህ መልዕክተኛ) የዳረኝ ከሰባቱ ሰማያት በላይ የሆነው አላህ ነው፡፡»

ከዘይነብ (ረ.ዐ) ልዩ መገለጫዎች መካከል ለርሷ ወሊይ (የጋብቻዋ ተያዥ ወይም ወኪልዋ) ሆኖ ለመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የዳራቸው ከሰማያቱ በላይ የሆነው ልዕለ ኃያሉ አላህ መሆኑ ነው፡፡ እርሷም የሞተችው በዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረ.ዐ) የኸሊፋነት ዘመን ጅማሮው ላይ ነበር፡፡

ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ (ረ.ዐ) መጀመሪያ ላይ የተዳረችው ለዘይድ ኢብን ሓሪሣ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ነበር፡፡ እርሱንም ያሳደጉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ፡፡ ዘይድም (ረ.ዐ) እርሷን በፈታት ጊዜ ኃያሉ አላህ እርሷን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዳራት፡፡ (ይህም የሆነበት ምክንያት) የጉዲፈቻ ልጆችን የቀድሞ ሚስቶቻቸውን ማግባት ፍቁድ መሆኑን ለኡምማው ለማሳየት ሲባል ነው፡፡

**ኡም-ሙ ሐቢባ (ረ.ዐ)**

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡም-ሙ ሐቢባን አገቧት፡፡ (ሙሉ) ስሟም ረምላ ቢንት አቢ ሱፍያን ሰኽር ኢብን ሐርብ አል-ቁረሺይ-ያ አል-አመዊይ-ያ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ያገቧት እርሷ አቢሲኒያ ውስጥ ስደተኛ ሆና ሳለች ነበር፡፡ ንጉሡ ነጃሺም ለርሷ መሕር (ይሆን ዘንድ) አራት መቶ ዲናርን ሰጡ፡፡ ከዚያም እርሷ ከዚያ ወደ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ታጅባ ተላከች፡፡ የሞተችውም በወንድሟ በሙዓዊያ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) የአገዛዝ ዘመን ነበር፡፡

**ሰፊይ-ያ (ረ.ዐ)**

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰፊይ-ያ ቢንት የይ-ዪ ኢብን አኽጠብን አገቧት፡፡ አኽጠብ የበኑ አን-ነዲር ጎሳ አለቃ ሲሆን፣ በኒ አን-ነዲርም የነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ወንድም የሆኑት የሃሩም ኢብን ዒምራን ተወላጆች ናቸው፡፡ ስለሆነም ሰፊይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) በአንድ በኩል የነብይ ልጅ ስትሆን በሌላ በኩል ደግሞ የነብይ ሚስትም ናት፡፡ ሰፊይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ከዓለማት ሴቶች ሁሉ እጅግ ቆንጆዋ ነበረች፡፡ ይሁንና ምርኮኛ ሆና ነበር፡፡ ከሴት ምርኮኞች መካከል ሆና ወደርሳቸው መጣች፡፡ ከባርነትም ነፃ አወጧት፡፡ ነፃነቷንም መሕሯ አደረጉላት፡፡ ይህም የሱንና ተግባር ሆኖ ተወሰደ፡፡

**መይሙና (ረ.ዐ)**

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መይሙና ቢንት አል-ሓሪሥ አል-ሂላሊይ-ያን አገቧት፡፡ እርሷ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል የመጨረሻዋ ስትሆን እርሳቸውም እርሷን ያገቧት ዑምራን ለማድረህ ወደ መካ ከተመለሱ በኋላ ነበር፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሞቱ ጊዜ ከሚስቶቻቸው መካከል ዘጠኙ በሕይወት እንደነበሩ በዑለሞች መካከል ምንም አለመግባባት የለውም፡፡ ከርሳቸው ሕልፈት በኋላም እርሳቸውን ለመከተል የመጀመሪያዋ ሚስታቸው በሂጅሪያ 20 የሞተችው ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ ነበረች፡፡ ከሚስቶቻቸው መካከል መጨረሻ ላይ የሞተችው ደግሞ ኡም-ሙ ሰለማ ስትሆን የሞተችውም በ62 ዓመተ ሂጅሪያ በየዚድ ኢብን ሙዓዊያ የኸሊፋነት ዘመን ነበር፡፡

# ክፍል 2 - የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ

# ከነብይነታቸው በፊት

**ውልደታቸው**

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተወለዱት በዝሆን ዓመት (ዓሙል ፊል - አብረሃ በዝሆን ሠራዊት አማካኝነት መካን ለማጥቃት በተንቀሳቀሰበት ዓመት)፣ በዕለተ ሰኞ፣ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል፣ ከሂጅራ 55 ዓመታት በፊት ሲሆን በግሪጎሪያን አቆጣጠር መሠረት በ571 ነበር፡፡ የዝሆን ሠራዊት ክስተትና አላህ እነርሱን መግታታቸው ኃያሉ አላህ ለራሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለተቀደሰው ቤቱ (ለከዕባ) ያስቀደመው ድል ነበር፡፡

**አባታ ቸው**

አባታቸው ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል ሙጧሊብ ናቸው፡፡ እርሳቸውም የሞቱት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተፀንሰው ሳሉ ነበር፡፡ ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወለዱት የቲም ሆነው ነበር፡፡

**እናታ ቸው**

እናታቸው ኣሚና ቢንት ወህብ ስትሆን ከበኑ ዙህራ ጎሳ ናት፡፡ እርሷም የሞተችው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰባት ዓመት ሳይሞላቸው በፊት ነበር፡፡

**አሳዳጊዎቻ ቸው**

እናታቸው ከሞቱ በኋላ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በኃላፊነት የተቀበሏቸው አያታቸው ዐብዱል ሙጠሊብ ነበሩ፡፡ ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 8 ዓመት ሲሞላ አያታቸውም ሞቱ፡፡ ከዚያም በአባታቸው በኩል የሚዛመዷቸው አጎታቸው አቡ ጧሊብ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በኃላፊነት ተቀበሏቸው፡፡ የአቡ ጧሊብ ስምም ዐብዱ መናፍ ነበር፡፡

**የጥቢ እናቶቻቸው**

**ሡወይባ**

አሳዳሪዋ አቡ ለሀብ ሲሆን በልጇ በመስሩሕ ወተትም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር አቡ ሰለማ ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል አሰድ አል-መኽዙሚይንም አጥብታለች፡፡ እንደዚሁም ከሁለቱ ጋር የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጉት የሆኑትን ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብንም አጥብታለች፡፡

**ሐሊማ አስ-ሰዕዲይ-ያ**

ሐሊማ የኡኒሳና የጁዛማ ወንድም በሆነው በልጇ ዐብዱሏህ ወተት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አጥብታለች፡፡ ኡኒሳ አሽ-ሸይማእ በመባልም ትታወቃለች፡፡ እነርሱም የአል-ሓሪሥ ኢብን ዐብዱል ዑዝ-ዛ ኢብን ረፋዓ አስ-ሰዕዲይ ልጆች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሐሊማ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የአጎታቸው ልጅ የሆነውን አቡ ሱፍያንም አጥብታለች፡፡

**አሳዳጊዎቻቸው**

| ሐሊማ ቢንት አቢ ዙአይብ አስ-ሰዕዲይ-ያ | የአቡ ለሀብ ባሪያ ሡወይብ | እናታቸው ኣሚና |
|---|---|---|

**ሸይማእ**

የሐሊማ ሴት ልጅና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጡት እህታቸው ናት፡፡ እርሷም ከሀዋዚን (ከመካ መከፈት በኋላ ከነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ውጊያን ካደረጉ ጎሳዎች መካከል አንዱ ከሆነው) ልዑካን ጋር ወደርሳቸው የመጣች ናት፡፡ እርሳቸውም ልብሳቸውን ዘረጉላት፡፡ ከርሳቸው ላይ ያላትን ሐቅ-ቋን ለመጠበቅ ሲሉም እዚያ ላይ አስቀመጧት፡፡

**አሳዳጊዎቻቸው**

**ኡም-ሙ አይመን**

ኡም-ሙ አይመን ሌላ ስሟ በረካ አል-ሐበሺይ-ያ ናት፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ከአባታቸው ወርሷታል፡፡ እርሷም አሳዳጊ እናታቸው ነበረች፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ለወዳጃቸው ለዘይድ ኢብን ሓሪሣ ዳሯት፡፡ ከዚያም ኡሳማ ኢብን ዘይድን ወለደችለት፡፡

ኡም-ሙ አይመን (ረ.ዐ) ያቺ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕልፈት በኋላ (ከዕለታት አንድ ቀን) አቡ በክር እና ዑመር (ረ.ዐ) የጎበኟት ናት፡፡ እርሷም አለቀሰች፡፡ እነርሱም «ምንድነው የሚያስለቅስሽ? ለመሆኑ አላህ ዘንድ ያለው ነገር ለመልዕክተኛው በላጭ አይደለምን?» አሏት፡፡ እርሷም «በእውነቱ አላህ ዘንድ ያለው ነገር ለመልዕክተኛው በላጭ መሆኑን በደንብ አውቃለሁ፡፡ በእውነቱ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከነበሩበት መልካም ይልቅ በላጭ ወደሆነው (መልካምነት) ተመልሰዋል፡፡ ይሁንና እኔ የማለቅሰው ከሰማይ የሆነው መለኮታዊ ራዕዩ ወደኛ (ከመውረድ) በመቋረጡ ምክንያት ነው» አለች፡፡ እነርሱም በለቅሶው ተቀላቀሏት፡፡ (ይህም ንግግሯ) እነርሱም ከርሷ ጋር እንዲያለቅሱ አደረጋቸው፡፡

**ሥራቸው**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እረኛ ሆነው ፍየሎችን አግደዋል፡፡ ይህም ለትዕግስታቸው፣ ለአቅመ ደካሞች ለሳዩት እዝነትና ስለነርሱም ኃላፊነትን በመሸከም ለከፈሉት (መስዋዕትነት) አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የፍየል እረኛ የሆነን እንጂ አላህ ሌላ ነብይን አልላከም፡፡ ባልደረቦቻቸውም (ረ.ዐ) «እርስዎም ቢሆኑ?» ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ «አዎን! እኔም በጥቂት ካራቶች ክፍያ ለመካ ሰዎች (ፍየሎችን) አግጃለሁ» አሉ፡፡»

**ሥራቸውና ትዳራቸው**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 25 ዓመት በደረሰ ጊዜ፣ ለንግድ ሥራ ብለው ወደሶሪያ መንገድ ወጡ (አመሩ)፡፡ ከቡስራ ጋርም ተገናኙ፡፡ ከዚያም ተመለሱ፡፡ በምልሰታቸው መጨረሻ ላይም የመጀመሪያ ሚስታቸው የሆነችዋን ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) አገቧት፡፡

**ከዕባን የመገንባቱ ሂደት**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 35 ዓመት በደረሰ ጊዜ ከዕባ ፈርሶ ነበር፡፡ ስለሆነም ቁረይሾች መልሰው ለመገንባት ተነሱ፡፡ የተለያዩ የቁረይሽ ጎሳዎችም ከዕባን ተከፋፍለው ለመሥራት ተስማሙ፡፡ እያንዳንዳቸውም በየፊናቸው የተለያዩ ኮርነሮችን ወሰዱ፡፡ ግንባታውም የጥቁሩ ድንጋይ ኮርነር ላይ በደረሰ ጊዜ ወደቦታው ማን ይመልስ በሚለው ጉዳይ ዙሪያ አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ አራት ወይም አምስት ቀናትን ቆዩ፡፡

.... ከዚያም በመስጊዱ በር በኩል በቅድሚያ የሚገባ ሰው በመካከላቸው ዳኝነትን እንዲሰጥ ተስማሙ፡፡ በቅድሚያ የገባ ሰውም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ፡፡ በመካከላቸውም ፍርድን እንዲሰጥ አደረጉ፡፡ እርሳቸውም ልብስ እንዲመጣ አዘዙ፡፡ ድንጋዩንም በርሱ ላይ አደረጉት፡፡ ከዚያም (ድንጋዩ) እቦታው እስከሚደርስ ድረስ ሁሉም ጎሳዎች (የልብሱን) ጠርዝ ይዘው እንዲሸከሙ አደረጉ፡፡ ከዚያም ራሳቸው በእጃቸው (ጥቁሩን ድንጋይ) ቦታው ላይ አስቀመጡት፡፡

**መገለላቸው**

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «መገለል (አል-ኸላእ ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/) ዘንድ ተወዳጅ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ወደ ሒራእ ዋሻ ይገለሉና እዚያም ይቆዩ ነበር፡፡ (እዚያም) ቁጥራቸው ለሚታወቅ ሌሊቶች ያህል (አላህን በብቸኝነት) ያመልኩ ነበር፡፡» እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ታቦታትና የሕዝቦቻቸው ዲንም የተጠላ ተደርገዋል፡፡ እርሳቸው ዘንድም ከነዚህ የበለጠ እጅግ የተጠላ ሌላ ነገር የለም፡፡

# የራዕዩ መውረድ ጅማሮ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 40 ዓመት በሞላ ጊዜ የነብይነት ብርሃኑ ከርሳቸው ላይ ደምቆ ነበር፡፡ ኃያሉ አላህም በዕለተ ሰኞ መልዕክቱን (በርሳቸው ላይ በማውረድ) አላቃቸው፡፡

ነብይነትን መቀበላቸው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) (የነብይነት ማዕረጋቸውን) በቀዳምነት እንዲጀምሩበት የተደረገው ነገር ቢኖር በእንቅልፍ ውስጥ (በሚገለጽ) መለኮታዊ ራዕይ በሆነው ጥሩ ሕልም (አማካኝነት) ነበር፡፡ (ስለሆነም) እንደ ንጋት ጎህ መቅደድ አምሳያ (እውነት) ሆኖ ቢመጣ እንጂ ሕልምን አያዩም ነበር፡፡ ከዚያም መገለል እርሳቸው ዘንድ ተወዳጅ ተደረገ፡፡ እናም ወደ ሒራእ ዋሻ ይገለሉና በርሱም ውስጥ ይቆዩ ነበር፡፡ ከዚያም ወደቤተሰባቸው ከመግባታቸውና ለዚህም (ዓላማ ዳግም) ስንቅን ይዘው ከመጓዛቸው በፊት ቁጥራቸው በውል ለሚታወቅ ሌሊቶች ያህል (እዚያው ሒራእ ዋሻ ውስጥ በመሰንበት አላህን በብቸኝነት) ያመልኩ ነበር፡፡ ከዚያም በሒራእ ዋሻ ውስጥ እያሉ እውነቱ (ሐቁ) እስኪመጣቸው ድረስ ወደ ኸዲጃ ይመለሱና ለተመሳሳዩ (ዓላማም) ይሰንቁ ነበር፡፡ (እውነቱ በመጣ ጊዜም) መላኢካው ወደርሳቸው መጣና ‹ኢቅራእ ወይም አንብብ› አላቸው፡፡ እርሳቸውም ‹እኔ ማንበብ አልችልም› አሉት፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡- ‹(መላኢካው) ያዘኝ፤ ከዚያም ጭንቀቴ ጥግ እስከሚደርስ ድረስ ጨመቀኝና ከዚያም ለቀቀኝ፤ ከዚያም (ዳግም) አንብብ› አለኝ፡፡ እኔም ‹(ዳግም) ማንበብ አልችልም› አልኩት፡፡ ከዚያም ያዘኝና ጥንቀቴ ጥግ እስከሚደርስ ድረስ ለሁለተኛ ጊዜ ጨመቀኝ፡፡ ከዚያም ለቀቀኝ፡፡ ከዚያም ‹(ለሦስተኛ ጊዜ) አንብብ› አለኝ፡፡ እኔም ‹ማንበብ አልችልም› አልኩት፡፡ ከዚያም ያዘኝ፤ ለሦስተኛ ጊዜም ጨመቀኝ፡፡ ከዚያም ለቀቀኝ፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ፡-

*«አንብብ! በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ! ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ፡፡ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን፡፡» (አል-ዐለቅ 96፡1-5)*

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ልባቸው እየተርገፈገፈ እነዚህን የቁርኣን አናቅጽ ይዘው ተመለሱ፡፡ ወደ ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ ገቡና ‹ሸፍኑኝ! ሸፍኑኝ!› አሉ፡፡ ፍርሃቱ እስከሚወገድላቸው ድረስም በልብስ ሸፈኑዋቸው፡፡ ለኸዲጃም የተከሰተውን ሁሉ ከነገሯት በኋላ ‹በእውነቱ ለሕይወቴ ፍርቻለሁ› አሏት፡፡ ኸዲጃም ‹አይሆንም! በአላህ እምላለሁ! አላህ እርስዎን ፈጽሞ አያዋርድዎትም፡፡ በእውነቱ ዝምድናን ትቀጥላህ፤ ረዳት የለሽን ትሸከማለህ፤ ድሃን ትመነዳለህ፤ እንግዳን ታሳርፋለህ፤ ከባድ አደጋ የደረሰባቸውንም ሰዎች በትክክል ታግዛለህ› አለቻቸው፡፡ ከዚያም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ወረቃ ኢብን ነውፈል ኢብን አሰድ ኢብን ዐብዱል ዑዝ-ዛ - የኸዲጃ የአጎቷ ልጅ ወደሆነው - ዘንድ ወሰደቻቸው፡፡ እርሱም በጃሂሊያው ዘመን ክርስትናን የተቀበለ ሰው ሲሆን፣የእብራይስጥ መጽሐፍንም ይጽፍ ነበር፡፡ አላህ እንዲጽፍ የፈቀደለትን ያህልም ኢንጂልን በእብራይስጥ ይጽፍ ነበር፡፡ ዕድሜው የገፉ አዛውንት ሲሆን ዓይኑም ታውሯል፡፡ ኸዲጃም (ረ.ዐ) ‹የአጎቴ ልጅ ሆይ! እስኪ የወንድምህ ልጅ የሚያወራውን አዳምጥለት› አለችው፡፡ ወረቃም ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ‹የወንድሜ ልጅ ሆይ! ምንድነው ያየኸው?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) የተመለከቱትን ነገር ነገሩት፡፡ ወረቃም ‹ይህ አላህ በሙሳ ላይ ያወረደው መላኢካ ነው፤ ዋ ምኞቴ! ምነው በዚህ ጊዜ ወጣት በሆንኩ? ዋ ምኞቴ! ሕዝቦችህ አንተን ከሀገርህ ሲያስወጡህ ሕያው በሆንኩ?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹እነርሱ ከሀገሬ ያስወጡኛል እንዴ?› አሉት፡፡ እርሱም ‹አዎን! አንድም ሰው አንተ ይዘህ የመጣኸውን ይዞ አልመጣም፤ ሕዝቦቹ ጠላታቸው አድርገው ቢይዙት እንጂ፡፡ ያንተ ጊዜ እኔ ላይ የሚደርስ ቢሆን፣ ከፍተኛ የሆነን እርዳታ እረዳህ ነበር፡፡ከዚያም ወረቃ ብዙም ሳይቆይ ሞተ፡፡ራዕዩም ለተወሰነ ጊዜ ተቋረጠ፡፡

## በነብይነት መመረጣቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ እየሄድኩ ሳለሁ በድንገት ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፡፡ እኔም ወደላይ ቀና ብዬ ተመለከትኩ፡፡ በዚህን ጊዜ ያንን በሒራእ የመጣብኝን መላኢካ በሰማይና ምድር መካከል (በሚሰፋ) ወንበር ላይ ተቀምጦ ተመለከትኩ፡፡ ከርሱም ፈራሁ፡፡ (ወደቤትም) ተመለስኩና ‹ሸፍኑኝ! ሸፍኑኝ!› አልኩ፡፡ ኃያሉ አላህም ቀጣዮቹን የቁርኣን አናቅጽ አወረደ፡-

*‹አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ተነሳ አስጠንቅቅም፡፡ ጌታህንም አክብር፡፡ ልብስህንም አጥራ፡፡ ጣዖትንም ራቅ፡፡› (አል-ሙድ-ደሥ-ሢር 74፡1-5)*

ከዚህ በኋላ መለኮታዊ ራዕዩ (ወሕዩ) እያየለና እየተከታተለ መምጣቱን ተያያዘው፡፡»

## የመለኮታዊ ራዕዩ ደረጃዎች

### 1/ እውነተኛ ሕልም

ይህም መለኮታዊ ራዕዩ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መውረድ የጀመረበት ሁኔታ ነው፡፡ እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብላለች፡- ‹እንደ ንጋት ጎህ (ደማቅ ሆኖ በገቢር) የሚመጣን እንጂ ሌላን ሕልም አይመለከቱም ነበር፡፡›

### 2/ ልባቸው ላይ በቀጥታ መግለጹ

አንዳንድ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መላኢካውን ሳያዩት እርሱ ግን እርሳቸውን በመንፈሳቸውና በቀልባቸው በኩል ያገኛቸው ነበር፡፡ እንዲህም ብለዋል፡- «ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) በመንፈሴ ውስጥ ነፋብኝ፤ እንዲህ እንዲህ ብሎም ነገረኝ ....»

### 3/ መልአኩ በሰው አምሳል መምጣቱ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዳንድ ጊዜ መላኢካው በሰው ቅርጽ ተመስሎ ወደኔ ይመጣና እኔንም ያናግረኝ ነበር፡፡ እኔም እርሱ የሚናገረውን ነገር እረዳ (እና አስታውስም) ነበር፡፡» መላኢካው በዚህ ሁኔታ ላይ ሲገለጽም ባልደረቦቻቸው አንዳንድ ጊዜ ይመለከቱት ነበር፡፡

### 4/ በሚያቃጭል ደውል

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዳንድ ጊዜ (መላኢካው) በሚያቃጭል ደውል መልክ ሆኖ ወደኔ ይመጣ ነበር፡፡ ይህም በኔ ላይ ከሁሉም እጅግ ከባዱ ነው፡፡ ከዚያም የነገረኝን ነገር (የተገለጸልኝን ነገር) ከጨበጥኩ በኋላ ይህም ሁኔታ ይለቀኝ ነበር፡፡» እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ በማለት አክላለች፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ቀዝቃዛ በሆነ ቀን ላይ መለኮታዊ ራዕዩ ሲገለጽላቸው አይቻለሁ፤ (እንዳለቀም) ያ ሁሉ (መጨናነቅ) ሲለቃቸውና ከግንባራቸውም ላይ ላብ ሲንጠባጠብ አስተውያለሁ፡፡» እንደዚሁም ራዕዩ በሚገለጽላቸው ጊዜ እርሳቸው መጓጓዣቸው ላይ ከሆኑ እንስሳዋ ትንበረከክ ነበር፡፡

### 5/ በተፈጥሮ ቅርጹ መገለጹ

አንዳንድ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራዕዩን ሲቀበሉ መላኢካውን በተፈጥሯዊ መልኩ ይመለከቱት ነበር፡፡ ከዚያም አላህ የፈቀደለትን ያህል ከራዕዩ ይገልጽላቸው ነበር፡፡ ይህም ልክ አላህ በሱረቱን ነጅም ውስጥ እንደገለጸው ሁለት ጊዜ በርሳቸው ላይ ተከስቷል፡፡

### 6/ ከአላህ የሆነ ቀጥተኛ ራዕይ

ይህም ኃያሉ አላህ በርሳቸው ላይ መልዕክቱን በቀጥታ ያወረደበት ሁኔታ ሲሆን እርሱም የሆነው ከሰባቱ ሰማያት በላይ በእርገት ሌሊት (በይለቱል ሚዕራጅ) ነበር፡፡ እንደ ሶላትና መሰል ጉዳዮችም ግዴታ ሆነው የተደነገጉት በዚህ ዓይነት ራዕይ አማካኝነት ነበር፡፡

### 7/ የአላህን ንግግር በመስማት

ይህም ልክ ኃያሉ አላህ ሙሳን (ዐለይሂስ-ሰላም) በቀጥታ እንዳናገራቸው ሁሉ እርሳቸውንም ያለ አገናኝ መላኢካ ኃያሉ አላህ በቀጥታ ባናገራቸው ወቅት የተከሰተ ነበር፡፡

**የመጀመሪያው ራዕይ**

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረደው የመጀመሪያው መለኮታዊ ራዕይ ቢኖር የሱረቱል ዐለቅ የመጀመሪያዎቹ አምስት አንቀፆች ናቸው:-

*«አንብብ! በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም:: ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም):: አንብብ! ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ:: ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን::» (አል-ዐለቅ 96:1-5)*

**የደዕዋቸው ደረጃዎች**

1. ነብይነት
2. የቅርብ ዘመዶችን ማስጠንቀቅ
3. ሕዝባቸውን ማስጠንቀቅ
4. እነዚያን ከዚህ በፊት ምንም አስጠንቃቂ ያልመጣላቸውን ሰዎች በሙሉ ማስጠንቀቅ - እነዚህ ሁሉም ዐረቦች ናቸው::
5. እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ከጋኔንና ከሰው ዘር ሆነው ጥሪያቸው (ደዕዋቸው) የደረሳቸውን በሙሉ ማስጠንቀቅ ነው::

**የደዕዋቸው እርከኖች**

1. **ምስጢራዊ ደዕዋ:-** ይህም እንደተላኩ ለመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት የቀጠለው ነበር
2. **ይፋዊ ደዕዋ:-** ይህም በልዕለ ኃያሉ አላህ እንዲህ እንዲያደርጉ በታዘዙ ጊዜ ነበር:- *«የታዘዝከበትንም ነገር በይፋ ግለጽ:: አጋሪዎችንም ተዋቸው::» (አል-ሒጅር 15:94)*

**የመጀመሪያዎቹ አማኞች**

| | |
|---|---|
| ከሴቶች ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) | ከወንዶች አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ (ረ.ዐ) |
| ከባርነት ነፃ ከተደረጉ ከአገልጋዮች ዘይድ ኢብን ሓሪሣ (ረ.ዐ) | ከታዳጊዎች ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ |
| ከባሮች ቢላል ኢብን ረባሕ አል-ሐበሺ (ረ.ዐ) ናቸው:: | |

**በኢስላም ቀዳሚ ከሆኑት ከፊሎቻቸው**

ከነዚያ ከላይ ከገለጽናቸው ቀዳሚ አማኞች በኋላ በርሳቸው በማመን ረገድ የርሳቸው ቤተሰብ አባላት የመጀመሪያዎቹ ናቸው:: ከዚያም ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፋን፣ ጦልሃ ኢብን ዑበይዲሏህ፣ አዝ-ዙበይር ኢብን አል-ዐው-ዋም፣ ሰዕድ ኢብን አቢ ወቅ-ቃስ፣ ዐብዱር ረሕማን ኢብን ዐውፍ፣ ኸብ-ባብ ኢብን አል-አረት፣ ሱሀይብ አር-ሩሚይ፣ ዐም-ማር ኢብን ያሲር እና እናቱ ሱመይ-ያ፣ አቡ ዑበይዳ ዓሚር ኢብን አል-ጀር-ራሕ፣ ዑሥማን ኢብን መዝዑን፣ አቡ ሰለማ ኢብን ዐብዱል አሰድ እና ዑትባ ኢብን ገዝዋን (ረዲየሏሁ ዐንሁም አጅመዒን) ናቸው::

# የመካው ምዕራፍ

## ጣዖታዉያኑ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸውን (ረ.ዐ) ማሰቃየታቸው

ጣዖታዉያኑ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ደዕዋን እውነተኝነትና የሰዎችን በርሳቸው ዙሪያ መሰብሰብን በተመለከቱ ጊዜ በአማኞች ላይ ከስቃዮች ሁሉ የከፋትን ስቃይ አድርሰዋል፡፡ አማኞችን ሲያሰቃዩ ከነበሩባቸው መንገዶች መካከልም ከፊሎቹ:-

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አስማተኛ እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ በማሰራጨት ሰዎች ከዙሪያቸው እንዲሸሹና እንዲፈሯቸው ማድረግ
- እርሳቸው እብድ እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ ማሰራጨትና በዚህም ሰዎች እርሳቸው ሞኝ እንደሆኑ አምነው እንዲቀበሉ ማድረግ
- እርሳቸው ውሸታም እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ ማሰራጨት፣ ይሁንና ይህ ውድቅ ሆነባቸው፤ ምክንያቱም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱ ዘንድ አስቀድሞ በእውነተኝነታቸውና በአማና ጠባቂነታቸው ሳቢያ በአል-አሚንነት (ታማኙ በመሆን) ይታወቁ ነበርና
- በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና እርሳቸው ይዘው በመጡት መልዕክት ላይ መሳለቅ፣ ማፌዝ
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰዎች ደዕዋ ለማድረግ በመጡ ቁጥር በማወክና በመረበሽ ሰዎችን መለኮታዊ ራዕዩንና ከሐቅ በኩል እርሳቸው የመጡበትን መልዕክት ከመስማት ማገድ
- በመካ መውጪያ በሮች ላይ ሆነው ለዑምራ ወይም ለሐጅ አልያም ከሁለቱ ውጭ ላሉ (ጉዳዮች ወደ መካ) የሚመጣን ሰው ተቀብለው ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማስጠንቀቅ
- በርሳቸው ላይ አካላዊ ጥቃትን ማድረስ፤ ዑቅባ ኢብን አቢ ሙዒጥ አንድ ጊዜ አቡ በክር (ረ.ዐ) ደርሰው እስከሚመልሱላቸው ድረስ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በልብሳቸው ይዟቸው እየጎተታቸው ሊያንቃቸው ቀረበ፡፡ (ሌላ ጊዜ ደግሞ) የግመል ፈርስን በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ወረወረባቸው፡፡ ከዚያም ልጃቸው ፋጢማ ከርሳቸው ላይ አንስታ አስወገደች፡፡
- ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል ማሴራቸው፣ ይህም የተከሰተው ወደአጎታቸው አቡ ጧሊብ ቀርበው እርሳቸውን በዐማራ ኢብን አል-ወሊድ እንዲለውጧቸውና ከዚያም እርሳቸውን ደግሞ (ለመግደል ዶልተው በጠየቁ ጊዜ) ነበር፡፡ ልክ እንደዚሁ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስደት ለመውጣት ባሰቡ ጊዜም እርሳቸውን ለመግደል ሞክረው ነበር፡፡
- ከአማኞች መካከል ደካሞች የሆኑትን በቅጣት ማሰቃየትና ክፉኛ ማስቸገር፣ ይህም ልክ በቢላል ሆድ ላይ የድንጋይ ቋጥኝን እንዳስቀመጡት፣ እንደዚሁም ልክ የዐም-ማር ቤተሰቦች ላይ እንዳደረጉትና በሌሎችም ላይ እንዳደረጉት ነበር፡፡

## ወደ ሐበሻ የተደረገው ስደት

የአማኞች ቁጥር በጨመረና አጋሪያንም እነርሱን መፍራት በጀመሩ ጊዜ በሙስሊሞች ላይ የሚደርሰው ስቃይና መከራ በኃይለኛው ጨመረ፡፡ ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊሞች ወደ ሐበሻ ይሰደዱ ዘንድ ፈቀዱላቸው፡፡እንዲህም አሉ:-

*«በእውነቱ (በሐበሻ) ውስጥ ሰዎች እርሱ ዘንድ የማይበደሉበት ንጉሥ አለ፡፡»*

## ወደ ሐበሻ የተደረገው ስደት

### የመጀመሪያው ስደት

በመጀመሪያው ስደት 12 ወንዶችና 4 ሴቶች ወደ ሐበሻ ተሰደዱ፡፡ ከነርሱም መካከል አንዱ ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፉን (ረ.ዐ) ነበሩ፡፡ እርሳቸውም መጀመሪያ ላይ የወጡ ነበሩ፡፡ ከርሳቸው ጋር ሚስታቸው ሩቀይ-ያ፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ የሆነችው ነበረች፡፡ እነርሱም ምርጥ በሆነ ጎርብትና ሐበሻ ውስጥ መኖር ጀመሩ፡፡ ከዚያም ቁረይሾች እስልምናን ተቀብለዋል የሚል (ዜና) ደረሳቸው፡፡ ይሁንና ይህ የውሸት ዜና ነበር፡፡ ከዚያም ወደመካ ተመለሱ፡፡ በተመለሱ ጊዜም ሁኔታው በፊት ከነበሩበት በላይ የከፋ ሆነ፡፡ ከነርሱም መካከል (ወደ መካ) ተመልሰው ከመጡት (ዳግም ወደ ሐበሻ) ተመለሱ፡፡ የተወሰነው ስብስብ ደግሞ ወደ መካ ገባና ከቁረይሾች በኩልም እጅግ የከፋውን ስቃይ ተቀበለ፡፡ (ከሐበሻ ተመልሰው ወደ መካ) ከገቡት መካከልም ዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) አንዱ ነበሩ፡፡

### ሁለተኛው ስደት

በዚህን ጊዜ 83 ወንዶችና 18 ሴቶች ስደት የወጡ ሲሆን እነርሱም ከንጉሥ አን-ነጃሺ ዘንድ በምርጥ ሁኔታ ሰፈሩ፡፡ ይህም (ዜና) ቁረይሾች ዘንድ ደረሰ፡፡ ከዚያም ዐምር ኢብን ዓስ እና ዐብዱሏህ ኢብን አቢ ረቢዓን ከተሟላ ስብስብ ጋር አድርገው (ሙስሊሞችን) ከአን-ነጃሺ ጋር ለማጣላት ሴራ ያሴሩ ዘንድ ላኳቸው፡፡ ሆኖም ግን ኃያሉ አላህ የነርሱን ሴራ በፊታቸው ላይ መለሰባቸው (ያሴሩት ሴራ ከሸፈባቸው)፡፡

## የዑመርና ሐምዛ መስለም

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነብይነት ከተላኩ በ6ኛው ዓመት አጎታቸው ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ እስልምናን ተቀበሉ፡፡ ሀምዛ የቁረይሽ ኃያላን (ጀግኖች) ሁሉ አለቃ ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ አላህም በሀምዛ አማካኝነት መልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ኃያል አደረጋቸው፡፡ ከዚያም በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዱዓ በረከት ዑመር ኢብኑል ኸጧብም እስልምናን ተቀበሉ፡፡በዚህን ጊዜ አማኞች ኃይልን አገኙ፡፡ከቁረይሾች ጥቃትም ዳኑ፡

## የአቡ ጣሊብ ሸለቆ

ከቁረይሾች በኩል በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የሚደርሰው ስቃይ ይባሱኑ ከፋ፡፡ ለሦስት ዓመታት ያክልም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ቤተሰቦቻቸውን በአቢ ጣሊብ ተራራማ መንገድ መሀከልም አግልለው አገቷቸው፡፡ ዐብዱሏህ ኢብን ዐብ-ባስም የተወለዱት በዚህ ተራራማ መንገድ ላይ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ አጋሪያኑ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከፍተኛ ስቃይን አደረሱ፡፡ በአርባ ዘጠኝ ዓመታቸውም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታግተው ከኖሩበት ስፍራ ሰብረው ወጡ፡፡

## የአቡ ጣሊብና የኸዲጃ ሞት

ታግተው ሲኖሩ ከነበረው ስፍራ ከወጡ ከጥቂት ወራት በኋላ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑት አቡ ጣሊብ በሰማንያ ሰባት ዓመታቸው ከዚህች ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ከዚያም ከአጭር ጊዜ በኋላ ከዲጃም በሞት ተለየቻቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ከአጋሪያኑ በኩል በርሳቸው ላይ ሲደርስ የነበረው ስቃይ ይባሱኑ ተፋፏመ፡፡

## ወደ ጧኢፍ መጓዛቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዘይድ ኢብን ሓሪሣ ጋር ሆነው ወደኃያሉ አላህ ለመጣራት ወደ አጥ-ጧኢፍ አመሩ፡፡ እዚያም የተወሰኑ ቀናትን ቆዩ፡፡ ሆኖም ግን ሰዎቹ መልዕክቱን ውድቅ አደረጉት፡፡ ይልቁንስ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አጠቁት፡፡ ከሀገራቸውም አስወጡት፡፡ ቁርጭምጭሚታቸው እስከሚደማ ድረስም በድንጋይ ወገሯቸው፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መካ ለመመለስ ከነርሱ ዞረው ተመለሱ፡፡ ከዚያም በአል-ሙጥዒም ኢብን ዐዲይ-ይ ከለላ ሥር ሆነው ወደ መካ ገቡ፡፡

**የዐድ-ዳስ መስለም**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በደርሶ መልስ ጉዞአቸው መንገድ ላይ ከዐድ-ዳስ ጋር ተገናኙ፡፡ እርሱም ክርስቲያን የነበረ ሲሆን በርሳቸውም አመነ፤ እውነተኛ መሆናቸውንም አረጋገጠላቸው፡፡

**የጋኔኖች ማመን**

እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመንገዳቸው ላይ ነኽላ በሚባል ቦታ ላይ ከጋኔኖች ጭፍራ የሆኑት ወደርሳቸው ዞሩ፡፡ ከነርሱ መካከልም ሰባቱ ከነሲቢን ወገኖች ነበሩ፡፡ እነርሱም ቁርኣኑን ሰሙ፤ እስልምናንም ተቀበሉ፡፡

**የሌሊት ጉዞውና እርገቱ**

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመንፈሳቸውና በሥጋቸው በሌሊት ጉዞ አማካኝነት ወደ መስጂድ አል-አቅሷ ተወሰዱ፡፡ ከዚያም በመንፈሳቸውና በሥጋቸው ወደአላህ ከሰባቱ ሰማያት በላይ አረጉ፡፡ ኃያሉ አላህም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አናገራቸው፤ አምስቱን ዕለታዊ ሶላቶችንም ግዴታ አድርጎ ደነገገባቸው፡፡

**እስልምናን ለተለያዩ ጎሳዎች ማቅረባቸው**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካ ውስጥ መኖራቸውን ገፉበት፡፡ እዚያም እስካሉ ድረስ የተለያዩ ጎሳዎችን ወደኃያሉ አላህ ይጠሩ ነበር፡፡ በየወቅቱ ወደነርሱ በመቅረብ የጌታቸውን መልዕክት እስኪያደርሱ ድረስ እንዲያስጠጓቸውና በአጸፋውም ጀነትን እንደሚመነዱ ይነግሯቸው ነበር፡፡ ይሁንና አንድም (የመካ አካባቢ) ጎሳ አልተቀበላቸውም፡፡ ኃያሉ አላህም ይህንን ክራማ (ክብር) (የእስልምና ፀጋን) ለአንሷር ጠብቆ አቆየ፡፡ (በዚሁ መሠረት በመካ ውስጥ ሳሉ) መልዕክቱ ከነርሱ መካከል ለስድስቱ ደረሳቸው፡፡ እነርሱም ለአላህና ለመልዕክተኛው ጥሪ ምላሽን ሰጡ፡፡ ወደ አል-መዲናም ተመለሱ፡፡ እስልምና በነርሱ ውስጥ እስከሚሰራጭና ከአንሷር ቤቶች መካከል የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሚወሳበት እንጂ ሌላ ቤት እስከማይኖር ድረስም ሕዝቦቻቸውን ወደ እስልምና ተጣሩ፡፡

**አንሷሮችና የዐቀባው ቃል ኪዳን**

**የመጀመሪያው የታማኝነት ቃል ኪዳን**

ከዚያም በቀጣዩ ዓመት ከአንሷር የሆኑ 12 ሰዎች፣ ከነርሱ መካከል አምስቱ ከመጀመሪያዎቹ ስድስት ሰዎች መካከል የነበሩ ሲሆኑ፣ ወደ መካ መጡና ዐቀባ ላይ (በሚና) ሱረቱል ሙምተሒና (በነርሱ ሳቢያ) በወረደችባቸው ሴቶች ቃል ኪዳን ላይ ሆነው ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የታማኝነት ቃል ኪዳንን ፈጸሙ፡፡ ከዚያም እነርሱ ወደ አል-መዲና ተመለሱ፡፡

**ሁለተኛው የታማኝነት ቃል ኪዳን**

በቀጣዩ ዓመት 73 ወንዶችና 2 ሴቶች ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡና እነርሱም የመጨረሻው የቃል ኪዳን ሰዎች ሲሆኑ፣ ልክ የገዛ ሴቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና ነፍሶቻቸውን ከጥቃት እንደሚከላከሉ ሁሉ ለአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ሊከላከሉላቸው ዘንድ የታማኝነት ቃል ኪዳንን ፈጸሙ፡፡ ከዚህ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው ወደነርሱ (አል-መዲና) ተጓዙ፡፡ ከነርሱም መካከል 12 አለቆችን መረጡ፡፡

# የመዲናው ምዕራፍ

### የስደት ፍቁድነት

ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለባልደረቦቻቸውንም (ረ.ዐ) ወደ አል-መዲና እንዲሰደዱ ተፈቀደላቸው:: ስለሆነም እነርሱ ትኩረት እንዳይደረግባቸው ዘንድ በምስጢር እየተከለሉ ወጡ:: ከነርሱ መካከልም የመጀመሪያው አቡ ሰለማ ዐብዱል አሰዲ አል-መኽዙሚ ነበር ተብሏል:: ሙስዐብ ኢብን ዑመይርም ነበር ተብሏል:: (የሆኖ ሆኖ) እየተከፋፈሉ (ከፊል ከፊል እየሆኑ) ወደ አንሷሮች አመሩ:: አንሷሮችም እነርሱን አስጠጓቸው:: ረዱቸውም:: እስልምናም በአል-መዲና ውስጥ ተስፋፋ (ተሰራጨ)::

የኋላ ኋላም ለአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ስደት ተፈቀደላቸው:: እርሳቸውም በዕለተ ሰኞ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል ውስጥ ለስደት ከመካ ወጡ:: በዚህን ጊዜ ዕድሜያቸው 53 ዓመት ነበር:: ከርሳቸውም ጋር አቡ በክር (ረዲየሏሁ ዐንሁ)፣ የአቡ በክር አገልጋይ የሆነው ዐሚር ኢብን ፋህይራ እና መንገድ መሪያቸው የሆነው ዐብዱሏህ ኢብን ኡረይቂጥ አል-ለይሲ ነበሩ:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና አቡ በክርም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ሠውር ዋሻ ገቡ:: እዚያም ውስጥ ሦስት ቀናትን ቆዩ:: ከዚያም በጠረፍ በኩል ጉዞአቸውን ቀጠሉ::

### ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና መግባታቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከርሳቸው ጋር የነበሩ ሰዎች መዲና በደረሱ ጊዜ - ዕለቱ ሰኞ ሲሆን ረቢዑል አው-ወል ወር አስራ ሁለት ቀናት አልፈው የነበረ ሲሆን - በኒ ዐምር ኢብን ዐውፍ ዘንድ የመዲና ከፍታ በሆነው ቁባእ ላይ አረፉ:: እነርሱም ዘንድ ለ14 ቀናት ቆዩ::

### የመጀመሪያው መስጂድ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና እንደገቡ የቁባእ መስጂድን ገነቡ:: ኢብን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል:- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በየእያንዳንዱ ቅዳሜ በእግራቸው እየተራመዱ አልያም በመጓጓዣቸው እየጋለቡ ወደ ሙስጂድ ቁባእ ይመጡ ነበር::» ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸውም ተዘግቧል:- «ቁባእ መስጂድ ውስጥ የሚሰገድ ሶላት ልክ ዑምራ እንደማድረግ ነው::»

### መስጂዱ አን-ነበዊን መገንባታቸው

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሴት ግመላቸውን ተሳፍረው (በመዲና መንገዶች) ላይ መጓዝ ጀመሩ:: (የመዲና) ሰዎችም እርሳቸው መጥተው እነርሱ ዘንድ እንዲያርፉ በመጠየቅ ያናግሯቸው ነበር:: የግመላቸውን ልጓምም ይይዙ ነበር:: እርሳቸውም «እርሷ (የት ማረፍ እንዳለባት) ታዛለችና መንገዷን ልቀቁላት» ይሉ ነበር:: ግመሏም ዛሬ መስጂዳቸው ያለበት ቦታ ላይ (ስትደርስ) ተንበረከከች:: ቦታውም (የግመሎችና ሌሎችም እንስሳት መቆሚያ ሲሆን) ከበኑ አን-ነጅ-ጃር መካከል የሆኑት፣ ሰህልና ሱሀይል የሚባሉ ሁለት ታዳጊ ልጆች ይዞታ ነበር:: ከዚያም አቡ አይ-ዩብ አል-አንሷሪ (ደጅ ሲደርሱ) ከግመላቸው ላይ ወረዱ:: ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸው (ረዲየሏሁ ዐንሁም) እዚያው (የግመሎች መቆሚያ ቦታ ላይ) ከጭቃ በሆነ ብሎኬትና በዘምባባ ቅጠል አማካኝነት መስጂዳቸውን (መስጂድ አን-ነበዊን) ገነቡ:: ከዚያም በመቀጠል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን ቤትና የሚስቶቻቸውንም ቤቶች ከመስጂዱ ጀርባ ሠሩ:: ከቤቶች ሁሉ ለመስጂዳቸው ይበልጥ ቅርብ የሆነውም የእመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ቤት ነበር:: ከዚያም ከሰባት ወራት በኋላ ከአቡ አይ-ዩብ ቤት ወጥተው ወደርሷ ቤት አመሩ::

**ወንድማ-ማችነት**

መስጂድን ከገነቡ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሙሃጂሩን፣ እነዚያ በቁጥር 90 በነበሩትና በአንሷሮች (እነዚያ ከሙሃጂሩን በብዙ እጥፍ በሚበልጡት) መካከል ኢስላማዊ ወንድማማችነትን መሠረቱ። እነርሱም እስከ በድር ዘመቻ ድረስ እርስ በርሳቸው ይወራረሱ ነበር።

**አይሁዶች**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ አል-መዲና በመጡ ጊዜ አይሁዶች እርሳቸውን አይተዋል። እርሳቸውም እውነተኛው የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን አውቀዋል። እርሳቸውም ያ እነርሱ ዘንድ በተውራት ተጽፎ የሚያገኙት መሆናቸውን ደርሰውበታል። ይሁንና ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነርሱ መካከል ጥቂት ጭፍሮች እንጂ ሌሎች እስልምናን አልተቀበሉም። ከነዚህም አንዱ ይበልጥ ዐዋቂያቸውና ሊቃቸው የነበረው ዐብዱሏህ ኢብን ሰላም ነበር። ይሁንና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለአይሁድ ጉሳዎች ራሱን የቻለ የቃል ኪዳን ስምምነት አረቀቁላቸው። እነዚህም ጎሳዎች በኑ ቀይኑቃዕ፣ በኑ አን-ነዲር እና በኑ ቁረይዛ ነበሩ።

**የቂብላ መቀየር**

በሌሊት ጉዞ ወቅት ሶላት ግዴታ ከተደረገች በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ በይቱል መቅዲስ ዞረው ይሰግዱ ነበር። ይሁንና ቂብላቸው ወደከዕባ እንዲቀየርላቸው ይፈልጉ ነበር። ይህንኑ በመከጀልም ፊታቸውን ወደሰማይ ያዞሩ ነበር። ስለሆነም አላህ ቀጣዩን አንቀጽ አወረደባቸው፡- *«የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን። ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር። የትም ስፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ።» (አል-በቀራ 2፡144)* ይህም በመሆኑ ከሂጅሪያ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቂብላቸውን (የሶላት አቅጣጫው) ወደከዕባ አዞሩ።

**የተጋድሎ መፈቀድ**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አል-መዲና አን-ነበዊይ-ያ ውስጥ ከሰፈሩና አንሷሮችም ለርሳቸው ሰብአዊ ጥበቃን ካደረጉላቸው በኋላ አላህ ቀጥሎ ያሉትን የቁርኣን አንቀጾች አወረደ፡- *«ለእነዚያ ለሚገደሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው። አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት። ... » (አል-ሐጅ 22፡39-40)*

በዚህም መሠረት ኃያሉ አላህ ለአማኞች እነርሱን ከሚዋጉ ጣዖታዊያን ጋር እንዲዋጉ (ተጋድሎ እንዲያደርጉ) ፈቀደላቸው። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎች መካከልም የመጀመሪያዎቹ የአል-አብዋእ፣ የቡዋጥ፣ የዑሺራና በከፊል ወደ አስ-ሰራያ የተደረጉ ዘመቻዎች ተጠቃሾች ናቸው።።

**የበድር ዘመቻ**

ከሂጅራ በኋላ በሁለተኛው ዓመት በወርሃ ረመዷን ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአማኞች የሆኑና ሦስት መቶ አስራ ምናምን የሆኑ ሰዎችን ይዘው ከመዲና ወጡ። (የዚህም ምክንያቱ) ከሶሪያ የሚመለሱ የቁረይሾችን የንግድ ቅፍለት ፍለጋ ነበር። ይሁንና አቡ ሱፍያን በሌላ መንገድ ዞሮ በመሄድ ቅፍለቱን አስመለጠ። ዳሩ ግን ሸይጣን ቁረይሾችን አታለላቸውና እነርሱም አማኞችን ለመውጋት (የጦር ኃይላቸውን ይዘው) ወጡ። ሁለቱም (አማኞችና ከሀዲዎች) በበድር ላይ ተገናኙ። ይህም ታላቁ የበድር ጦርነት ሆነ። (የበድር ጦርነትም) ያ በሌላ ስሙ ‹የውመል ፉርቃን› (የመለያያ ቀን) ተብሎ የተሰየመው ነበር።

ሁለቱ ሠራዊቶች ለመፋለም በአውደ ውጊያ ግንባር በተገናኙ ጊዜ፣ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወደርሱ በመተናነስ ጌታቸውን (በኃይለኛው) ለመኑ። ስለሆነም ኃያሉ አላህ ከነርሱ ጋር ይዋጉ ዘንድ አማኞችን በመላእክት አማካኝነት አበረታቸው። ኃያሉ አላህ በከሀዲያን ሕዝቦች ላይም ድልን አጎናጸፋቸው። ቃሉንም የበላይ አደረጋት። በበድር ጦርነት ላይም ከአጋሪያን መካከል ሰባ ሰዎች ተገደሉ። ከአማኞች መካከል ደግሞ አስራ አራት ሰዎች የሰማዕትነት ደረጃን አገኙ።

**የቀይኑቃዕ ዘመቻ**

በ3ኛው ዓመተ ሂጅሪያ የበኑ ቀይኑቃዕ ሰዎች የእርቀ ሰላም ቃል ኪዳናቸውን አፈረሱ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ለ15 ሌሊቶች ያክል እነርሱን በጦር ኃይል ከበባ ውስጥ አስገቧቸው፡፡ ከዚያም በርሳቸው ብያኔ መሠረት እጃቸውን ሰጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱን ከሀገራቸው አስወጧቸው፡፡ እነርሱም በቁጥር ሰባት መቶ ነበሩ፡፡

**የኡሑድ ጦርነት**

የኡሑድ ዘመቻ የተካሄደው በሸው-ዋል ወር ውስጥ ሲሆን ቁረይሾቹ በበድር ጦርነት የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀል ሲሉ ወደ ሦስት ሺ የሚጠጋ ሰው ይዘው ወደ መዲና ወጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ወደ ሰባት መቶ የሚጠጋ ሰው ይዘው ወደ ኡሑድ ወጡ፡፡ ሙናፊቆቹ ግን ከጦራቸው መካከል የተወሰነውን ገንጥለው ተመለሱ፡፡

በቀኑ መጀመሪያ አካባቢ ኳሏ (ስለቱ) ለሙስሊሞች ሆና ነበረ፡፡ ከዚያም ኃያሉ አላህ ሙስሊሞችን ሞከራቸውና የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ነጥለው የጥቃታቸው ዒላማ እስከሚያደርጉ ድረስም ኳሏን (ስለቱን) ወደሙሽሪኮች እጅ መለሰ፡፡ ስለሆነም ግንባራቸውን አቆሰሉ፡፡ የፊት ጥርሳቸውንም ሰበሩ፡፡ በዚያን ዕለት መላኢኮች ከርሳቸው ጋር ተዋጉ፡፡ ከርሳቸው ባልደረቦች መካከልም ሰባዎቹ ተሰው (የሰማዕትነት ክብርን ተጎናጸፉ)፡፡ ከነርሱም መካከል ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ፣ ሙስዐብ ኢብን ዑመይር፣ አነስ ኢብን አን-ነድር፣ ሐንዘላ አል-ገሲል እና ከነርሱ ውጭ ያሉትም ሰማዕት ሆኑ፡፡ በዚያን ዕለት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ እስኪሉ ድረስ አቢ ጦልሓ ኢብን ዑበይዱሏህ በታላቅ ጀግንነት ተዋጋ፡- «ጀነት ለጦልሓ ተገቢው ሆነች፡፡»

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ሙስሊሞቹ ዳግም ለተመሳሳይ ዓላማ ተሰባሰቡ፡፡ አላህም የሙሽሪኮችን እጅ ከነርሱ ላይ ከለከለ፡፡

የኡሑድ ዕለት የመሞከሪያና የመከበቢያ ዕለት ነበር፡፡ ኃያሉ አላህም በዚያች ዕለት ሙእሚኖችን ሞከራቸው፡፡ ሙናፊዎችንም ግልጽ አደረጋቸው፡፡ የሻቸውንም ሰዎች በሰማዕትነት አማካኝነት አላቃቸው፡፡

ከዘመቻው በኋላ ቁረይሾቹ ሙስሊሞችን ከናካቴው ለመጨረሽ ፈልገው ዳግም ተመልሰው እየመጡ መሆናቸውን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሙ፡፡ ስለሆነም ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከአማኞቹና ከቁስለኞቻቸው ጋር ሆነው ወደነርሱ አቅጣጫ አመሩ፡፡ ሙስሊሞቹም ሐምራአል አሰድ በደረሱ ጊዜ ይህም (ድርጊታቸው) ቁረይሾች ዘንድ ደረሰ፡፡ ከዚያም ተገነጣጠሉ፡፡ ወደ መካም ተመለሱ፡፡

**ከሂጅራ በኋላ 4ኛው ዓመት**

በአራተኛው ዓመተ ሂጅራ ቢእር መዑና በተባለ ቦታ አንድ ክስተት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይኸውም ከሰሓቦች መካከል 70 የሚሆኑት፣ እነዚያ በቁርኣኑ እጅግ አዋቂዎች የሆኑት የተገደሉበት ቦታ ሆነ፡፡ እንደዚሁም የበኑ አን-ነዲር ዘመቻ ተደርጎ ነበር፡፡ እነዚህም እነዚያ ኃያሉ አላህ በልቦቻቸው ውስጥ ፍርሃትን እስከሚለቅባቸው ጊዜ ድረስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጦር ከበባ ሥር አስገብቷቸው የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱን ከአል-መዲና አስወጧቸው፡፡ ሱረቱል ሐሽርም የወረደችው እነርሱን በማስመልከት ነበር፡፡

**የሙረይሲዕ ዘመቻ**

በአምስተኛው ዓመተ ሂጅራ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኒ አል-ሙስጠሊቅን ለመዋጋት ወጡ፡፡ የድል ባለቤትም ሆነው ተመለሱ፡፡ በዚህ ጉዞ ወቅትም አት-ተየም-ሙም ተደነገገ፡፡ በእመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ላይ የተወራው ቅጥፈትም ተከሰተ፡፡ ይህም የተገኘው ሙናፊቆቹ የሙእሚኖች እናት በሆነችው ዓኢሻ ላይ ውሸትን በቀጣጠፉበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁንና እርሷ የንጽሕቶች ሁሉ ንጽሕት ናት፡፡ ስለሆነም ኃያሉ አላህ ንጽሕነቷን ሱረቱን ኑርን አውርዶ እስከሚያረጋግጥላት ድረስ ይህ ጉዳይ በርሷና በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሊቋቋሙት ዘንድ ሲበዛ ጠንቶባቸው ነበር፡፡ (እውነቱ በተገለጠ ጊዜም) እነዚያ የቅጥፈት ዜናውን ያሰራጩ ሰዎችም በጅራፍ ተገረፉ፡፡

## የአሕዛብ ዘመቻ

የኸንደቅ (የቦዩ) ወይም የአሕዛብ ዘመቻ የተካሄደው በወርሃ ሸው-ዋል ከሂጅራ በኋላ በስድስተኛው ዓመት ነበር፡፡ በዚህን ወቅት አይሁዶቹ ቁረይሾችንና ማንኛውንም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸውን ለመውጋት በመሐላ ከሚያረጋግጥላቸው አካል ሁሉ ጋር ተስማሙ፡፡ የቁረይሾቹ ኃይል ከበኑ ሱለይም፣ ከበኑ አሰድ፣ ከፈዛረህ፣ ከአሽጀዕ እና ከነርሱም ውጭ ካሉት ኃይሎች ጋር ተጣምሮ አስር ሺ ሰው በያዘ (ጥምር የጦር ኃይል) ወደ መዲና መጣ፡፡

ሰልማን አል-ፋሪሲ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እነርሱን ከጥምር ኃይሎቹ መከላከል የሚያስችላቸውን ቦይ (ጉድጓድ) እንዲቆፈሩ ዘንድ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምክርን ለገሱ (አመላከቱ)፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሦስት ሺ ሰው ይዘው (ለጦርነት) ወጡ፡፡ የሰልዕ ተራራንም ከበስተ ጀርባ በኩል እንደ መከላከያ ግንብ ተጠቀሙ፡፡ ቦዩን ደግሞ ከፊት ለፊታቸው እንደ መከላከያ ተጠቀሙበት፡፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የሰላም ስምምነት ፈጥረው ሲኖሩ የነበሩ ቁረይዛዎችም ዳግም ከርሳቸው የደህንነት ዋስትናን ጠየቁ፡፡ ካልሆነ ግን የታማኝነት ቃል ኪዳናቸውን ሊያፈርሱና (እርሳቸውን ለመውጋት ሲሉ) ከጥምር የጦር ኃይሉ ጋር ሊቀላቀሉ ሆነ፡፡

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኑዐይም ኢብን መስዑድን ወደ በኑ ቁረይዛዎችና ወደ ጥምር ኃይሎቹም ላኩት፡፡ እርሱም በነርሱ ደረጃ ላይ ሆኖ ከነርሱ ጋር ሴራን ጎነጎነ፡፡ የኋላ ኋላም በመካከላቸው ነገሮችን አበለሻሸ፡፡ ከዚያም ኃያሉ አላህ ከነፋስ የሆነን ሠራዊት ላከባቸው፡፡ ነፋሷም ካምፖቻቸውን አፈራረሰችባቸው፡፡ የማብሰያ ዕቃዎቻቸውንም ላዩን ወደታች ገለባበጠችባቸው፡፡ እነርሱም በነፋሱ ኃይል ተንቀጠቀጡ፡፡ በልቦቻቸው ውስጥም ፍርሃትን ጣለችባቸው፡፡ ጥምር ኃይሎቹንም በታተነቻቸው፡፡ በስተ መጨረሻም ያ ሁሉ ሴራ ምንም ሳይፈይዳቸው ተመልሰው ወደሀገራቸው ሄዱ፡፡

ከዚያ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደበኑ ቁረይዛ ዘመቱና በነርሱም ጉዳይ ላይ ዳኝነትን ይሰጥ ዘንድ ሰዕድ ኢብን ሙዓዝን ሾሙ፡፡ ሱረቱል አሕዛብም የወረደችው ይህንኑ ዘመቻን በማስመልከት ነበር፡፡

## የሑደይቢያ ስምምነት

ከሂጅራ በኋላ በስድስተኛው ዓመት ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሺ አራት መቶ ከሚሆኑ ባልደረቦቻቸው ጋር ዑምራ ለማድረግ አስበው ወጡ፡፡ አል-ሑደይቢያ በደረሱ ጊዜም ቁረይሾች እነርሱን ወደ መካ ከመግባት ከለከሏቸው፡፡ ለአስር ዓመታት ያክልም ከነርሱ ጋር የጦርነትን መዘዝ ለመተው የሚያስችል የሰላም ስምምነትንም እንዲሰጧቸው ጠየቋቸው፡፡ ይህም ልክ ኃያሉ አላህ እንዳለው ለሙእሚኖች ታላቅ ድል ሆነ፡-

*«እኛ ላንተ ግልጽ የኾነን መክፈት ከፈትንልህ፡፡» (አል-ፈትሕ 48፡1)*

ይህ የሰላም ስምምነትም ካስገኛቸው (ድሎች መካከል) ቁረይሾቹ ለሙስሊሞች በቀጣዩ ዓመት ወደ መካ ተመልሰው በመግባት ዑምራ እንዲያደርጉ መፍቀዳቸው ነበር፡፡ ይህም በዙል ቂዕዳ ውስጥ ለስድስተኛ ዓመተ ሂጅራ የማካካሻ ዑምራ ወይም ‹ዑምራ አል-ቀዳእ› ሆነ፡፡

## የኸይበር ዘመቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአል-ሑደይቢያ ከተመለሱ ከ20 ቀናት በኋላ፣ ወደ ኸይበር ለመዝመት ወጡ፡፡ ኸይበር ከአል-መዲና በስተ ሰሜን በኩል የምትገኝ ስትሆን እዚያም ሙስሊሞቹ አይሁዶችን በግምት ለሀያ ቀናት ያክል በጦር ኃይል ከበባ ሥር አስገቧቸው፡፡ በኸይበር ውስጥ ሙስሊሞችም ኃይለኛ ትግልን አካሄዱ፡፡ አይሁዶቹም በሚደርስባቸው ጥቃት ሳቢያ እንደሚጠፉ እርግጠኞች በሆኑ ጊዜ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርቀ ሰላምን ጠየቁ፡፡

ከዚያም ደማቸውን አስጠብቀው የለበሱትን ልብሶች ብቻ ይዘው እንዲወጡ ተስማሙ፡፡ ከዚያም ከመሬታቸው ከሚወጣው ነገር ግማሹን እየሰጡ በመሬታቸው ላይ እንዲሠሩበት በመስማማት ኃላፊነቱን ሰጧቸው፡

## የጀዕፈር መምጣት

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸይበር ሳሉ አቡ ሁረይራ ሙስሊም ሆነው ወደ አል-መዲና መጡ፡፡ ጀዕፈር ኢብን አቢ ጣሊብ፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአጎታቸው ልጅ የሆኑትና እነዚያ ከርሳቸው ጋር ሐበሻ ውስጥ ቀርተው የነበሩትም መጡና ነብዩንም (ሰ.ዐ.ወ) በኸይበር ሳሉ አስደሰቷቸው፡፡ እንደዚሁም ከነርሱ ጋር አቡ ሙሳ አል-አሽዐሪ እና ባልደረቦቻቸውም መጥተው (ከሙስሊሞች ጋር ተቀላቀሉ)፡፡

## የሙእጣ ዘመቻ

የሙእጣ ዘመቻ የተካሄደው ከሂጅራ በኋላ በስምንተኛው ዓመት ነበር፡፡ የዚህ ዘመቻ መነሻ ምክንያቱም ሸረሕቢል ኢብን ዐምር አል-ገስ-ሳኒ የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛ ወደ ሮማው ንጉሥ እያመራ ሳለ ገደላቸው፡፡ ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ሦስት ሺ የሚሆኑትን ላኩ፡፡ ወዳጃቸውን ዘይድ ኢብን ሓሪሣንም መሪያቸው አድርገው ሾሙ፡፡ እንዲህም አሉ፦ «ዘይድ በጦርነቱ ላይ ከተሰዋ ከዚያም ጀዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብ ሰዎቹን ይመራል፡፡ ይሁንና ጀዕፈርም በጦርነቱ ላይ ከተሰዋ ዐብዱሏህ ኢብን ረዋሓ ሰዎቹን ይመራል፡፡»

የሮማው ንጉሥ ሂረቅል እና እነዚያ ከርሱ ጋር የተሰለፉ የዐረብ ረዳት ጎሳዎች 200 ሺ የጦር ሠራዊት ይዘው ዘመቱ፡፡ ሁለቱም ኃይሎች ሙእጣ ላይ ተገናኙ፡፡ ውጊያም ተካሄደ፡፡እነዚያ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት ሹመት የተሰጣቸው ሰዎችም እንዳሉ ተሰው፡፡ ከዚያም ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድ የሙስሊሞችን ባንዲራ ያዘ፡፡ እርሱም የሙስሊሞችን ጦር በምርጥ ሁኔታ መራ፡፡ የኋላ ኋላም ሙስሊሞችን ከአላህ ጠላቶችና ከጠላቶቻቸው (የጦር ከበባ ሥር) ነፃ አውጥቶ ዳግም አንድ ላይ አሰባሰባቸው፡፡

## ታላቁ የመካ መከፈት ድል

በተመሳሳይ ዓመት በኑ በክር - እነርሱም ከቁረይሾች ጋር የሰላም ስምምነት ውል ያላቸው ሲሆኑ - በኑ ኹዛዓን - እነርሱ ደግሞ ከነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ጋር የሰላም ስምምነት ያላቸው ሲሆኑ - አጠቁ፡፡ ቁረይሾችም በዚህ ጥቃት ላይ እነርሱን በምስጢር አገዙ፡፡ ይህም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በደረሰ ጊዜ እርሳቸውም መካን ለመክፈት ቆርጠው ተነሱ፡፡ አቡ ሱፍያንም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለማናገር ወደ አል-መዲና መጡ፡፡ ሆኖም ግን እርሳቸው ከርሱ ምንም ነገር ለመስማት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ስለሆነም አቡ ሱፍያን ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ያነጋግሩለት ዘንድ አቡ በክርን፣ ዑመርንና ዐሊን አናገሩ፡፡ ግና ሁላቸውም እምቢ አሉ፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸው ወደነርሱ መዝመታቸውን እንዳያውቁ ዘንድ አላህ ቁረይሾችን ደንቆሮዎች እንዲያደርጋቸው ለመኑ፡፡ ኃያሉ አላህም ለዚህ ዱዓቸው ምላሽን ሰጠ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) አስር ሺ ሠራዊትን ይዘው ወደ መካ ዘመቱ፡፡ ወደ መካም ዘልቀው ገቡ፡፡ ይሁንና ከመካ መከፈት ትንሽ ቀደም ብለው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑት አል-ዐብ-ባስ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ እስልምናን ተቀበሉ፡፡

መካን በድል በከፈቱ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ ከነበሯቸው ነገሮች መካከልም፦ «ወደ አቡ ሱፍያን ቤት የገባ ሰው እርሱ ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ ወደመስጂድ የገባ ሰውም ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ በሩንም የዘጋ ሰው ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው» የሚሉት ንግግሮቻቸው ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸውን ለመውጋት ከተሸቀዳደሙ አካላት በስተቀር፣ እርሳቸውንና ሙስሊሞችን ካሰቃዩና ደማቸውንም ከንተ ካደረጉ ጥቂት አካላት በስተቀር ከማንም ጋር ተዋግተው አያውቁም፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መካ በገቡ ጊዜ ከዕባን ዞረዋል፡፡ ነገር ግን በኢሕራም ሁኔታ ውስጥ ሆነው አልነበሩም፡፡ ከዚያም ዑሥማን ኢብን ጦልሓን ጠሩትና የከዕባን ቁልፍ ተቀበሉት፡፡ ከዚያም በውስጡ ያሉትንና በዙሪያው ያሉትንም ጣዖታት በሙሉ ሰባበሩ፡፡ ከዚያም ቁልፉን ለዑሥማን መለሱለት፡፡ መካ በድል ከተከፈተች በኋላ ብዙ ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ፡፡ እንደውም ብዙ ጎሳዎች እስልምናን እየተቀበሉ በፍጥነት ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡ፡፡

ጣዖታትን ማውደማቸው

አላህ መካን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በድል ከከፈተላቸው በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦቻቸውን በመካ ዙሪያ ያሉትን ጣዖታት ሁሉ ያወድሟቸው ዘንድ ላኩአቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ሱዋዕን ያፈርስ ዘንድ ዐምር ኢብን ዓስን ላኩት፡፡ መናትን ያፈርስ ዘንድ ሰዕድ ኢብን ዘይድን ላኩት፡፡ አል-ዐዝ-ዛን ያፈርስ ዘንድ ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድን ላኩት፡፡ ዚል ከፍ-ፈይንን ያፈርስ ዘንድ አጥ-ጡፈይልን ላኩት፡፡ የጠይእ ታቦትን ያፈርስ ዘንድ ዐሊን ላኩት፡፡

## የሑነይን ዘመቻ

የሀዋዚን ጎሳ አባላት መካ በድል መከፈቷን በሰሙ ጊዜ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በታላቅ ሰልፍ ለመዝመት ተሰባሰቡ፡፡ ሁሉንም ንብረቶቻቸውን፣ ሴቶቻቸውንና ብዛታቸውን (ልጆቻቸውን) ከራሳቸው ጋር እየነዱ መጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) 12 ሺ ሠራዊትን ይዘው ወደነርሱ ዘመቱ፡፡ ሙስሊሞችም የሑነይን ሸለቆ እስከሚደርሱ ድረስ በቁጥራቸው ብዛት ተደነቁ፡፡ ይሁንና ሀዋዚኖች ሙስሊሞችን ባልገመቱት ቦታ ላይ አድፍጠው ድንገት አጠቁአቸው፡፡ ከድንጋጤው ኃያልነት የተነሳም ሙስሊሞቹ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እስኪሸሹ ድረስ ሀዋዚኖች ልክ እንደ አንድ ሰው ብርታት እጅግ በረቱባቸው፡፡ ከሙሃጂሮችና ከአህሉል በይት የሆኑ ውስን ጭፍሮች ግን ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፀንተው ቆሙ፡፡

ከዚያም ኃያሉ አላህ እነዚያን ያመኑትን ሰዎች አፀናቸውና ከዚያም ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ ተመለሱ፡፡ ኃያሉ አላህም በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እስኪያጎናጽፋቸው ድረስ ከርሳቸውም ጋር ተዋጉ፡፡ የኋላ ኋላም ሀዋዚኖቹ ወደ ጧኢፍ ሸሹ፡፡ ከዚህ በኋላ ከሀዋዚን ጎሳ የሆኑ 14 ሰዎች፣ እነዚያ እስልምናን የተቀበሉት፣ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡ፡፡ ከምርኮኞችም መካከል ቤተሰቦቻቸውን በውለታ መልክ እንዲመለሱላቸው ጠየቁ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ አደረጉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም (ረ.ዐ) ይህንኑ ከርሳቸው ጋር አደረጉ፡፡

## የጧኢፍ ዘመቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሀዋዚንን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ወደ ጧኢፍ ለመዝመት ወሰኑ፡፡ ጧኢፍ በደረሱ ጊዜም የነርሱን ምሽግ ለ18 ቀናት ያክል በጦር ኃይል ከበባ ሥር አስገቡት፡፡ ከዚያም ምንም ውጊያ ሳይገጥሙ ተመለሱ፡፡

## የተቡክ ዘመቻ

በዘጠነኛው ዓመተ ሂጅራ የተቡክ ዘመቻ (ገዝወቱል ዑስራ - አስቸጋሪው ዘመቻ) ተካሄደ፡፡ ዘመቻው የተካሄደው እጅግ ሞቃታማ በሆነ ወቅት ነበር፡፡ እንደዚሁም በፍራፍሬዎችና ጥላዎች ወቅት ነበር፡፡ በዚህም ሳቢያ ለዘመቻው መውጣት በሰዎች ላይ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻ ለማድረግ በሚፈልጉበት ጊዜ ሰሓቦችን ምጽዋት በመስጠት ያነሳሱ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፋን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ሦስት መቶ ግመሎችን ከነጭነቶቻቸውና ከኮርቻዎቻቸው ከአንድ ሺ ዲናር ጋር ለገሱ፡፡ በዚህን ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) «ዑሥማን ከዚህ ቀን በኋላ የሚሠራው ነገር እርሱን አይጎዳውም» አሉ፡፡ የተቀሩ ባልደረቦቻቸውም በአቅማቸው ልክ በአላህ መንገድ ላይ ለገሱ፡፡

ሙናፊቆቹ እንዳሉ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ከመዝመት ወደኋላ ቀሩ፡ ከምርጥ ባልደረቦቻቸው መካከልም ሦስቱ ያለ በቂ ምክንያት (እንዲሁ ወደኋላ ቀሩ)፡፡ እነርሱም ከዕብ ኢብን ማሊክ፣ ሂላል ኢብን ኡመይ-ያ እና ሚራራ ኢብን አር-ረቢዕ ነበሩ፡፡ ይሁንና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደመዲና በተመለሱ ጊዜ የቀሩበትን ምክንያት አስረዱ፡፡ ከሱረቱት ተውባ የሆኑ የተወሰኑ አንቀጾችም የወረዱት እነርሱን በማስመለከት ነበር፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«ለነዚያ ሦስት (ከነብዩ) ወደኋላ በቀሩት ላይ ..... » (አት-ተውባ 9፡118)*

ኃያሉ አላህም የሦስቱን ሰሓቦች እውነተኝነታቸውን ስለሚያውቅ ፀፀታቸውን ተቀብሎ በምሕረቱ ተመለሰላቸው፡፡ ይሁንና በዚህቹ ምዕራፍ ውስጥ ሙናፊቆችን አዋረዳቸው፡፡ ስለነርሱ በማውሳትም ምዕራፏን ቋጫት፡፡ ስለሆነም ምዕራፏ አል-ፋዲሓ (አጋላጭዋ) በሚል ተሰየመች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሙናፊቆችን ስላጋለጠች ነው፡፡

## የተቡክ ዘመቻ

በተቡክ ዘመቻ ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአይላ ሰዎች ጋር የሰላም ስምምነትን ፈጠሩ፡፡ ልክ እንደዚሁ ከጀርባና ከአዝረሕ ሰዎች ጋርም ፈጠሩ፡፡ለነሱም የስምምነት ውልን ጻፉላቸው፡፡ ልክ እንደዚሁ በሙስሊሞች ቃል ኪዳን ሥር ለመኖር ግብር መክፈል እንዳለባቸው በመስማማት ከኡከይደር ሰዎች ጋርም ስምምነትን ፈጠሩ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተቡክ 18 ቀናትንም ቆዩ፡፡ ከዚያም ምንም ውጊያ ሳይገጥሙ ወደመዲና ተመለሱ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደመዲና በተመለሱ ጊዜም አላህ ያን መናፍቃን የገነቡትን መስጂድ አድ-ዷራራን ያፈርሱ ዘንድ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፡-*«እነዚያም (ምእምናንን) ለመጉዳት፣ክህደትንም ለማበርታት፣ በምእምናንም መካከል ለመለያየት፣ ከአሁን በፊት አላህንና መልክተኛውን የተዋጋውንም ሰው ለመጠባበቅ መስጊድን የሠሩት (ከነሱ ናቸው)፡፡ … » (አት-ተውባ 9፡107)*

በዚሁ መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂዱን አፈራረሱት፡፡ ይህም እርሳቸው ራሳቸው የተሳተፉበት የመጨረሻው ዘመቻቸው ሆነ፡፡

## የልዑካን ቡድኖች

ከተቡክ ዘመቻ በኋላ ብዙ ጎሳዎች በልዑካን ቡድኖቻቸው አማካኝነት ኢስላምን ተቀበሉ፡፡ ስለሆነም ይህ 9ኛው ዓመተ ሂጅራም የልዕካኖች ዓመት ተብሎ ተሰየመ፡፡ የተለያዩ ጎሳዎች እስልምናን መቀበላቸውን እያወጁ በፍጥነት ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይመጡ ጀመር፡፡ ከነርሱም መካከል የበኑ ተሚም ልዑክና መሪያቸው ዐጣሪድ ኢብን ሓጂብ አት-ተሚሚይ፣ የጠይእ ልዑክ እና መሪያቸው ዘይድ አል-ኸይል፣ የዐብዱል ቀይስ ልዑክ እና መሪያቸው አል-ጃሩድ አል-ዐብዲይ እንዲሁም የበኑ ሐኒፋ ልዑክ ሲሆኑ፣ ከነርሱም ውስጥ ሐሰተኛው ሙሰይሊማ፣ ያ የኋላ ኋላ ነብይነት ይገባኛል በሚል የሞገተው ግለሰብ ይገኙበት ነበር፡፡

## የአቡበክር ሐጅ

ከሂጅራ በኋላ በ9ኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለነዚያ ሐጅ ለሚያደርጉ ሰዎች አቡ በክርን መሪያቸው አድርገው ላኳቸው፡፡ ለሰዎችም የሐጅ ሥርዓትን አቋቋሙ፡፡ እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰዎቹ የሱረቱ አት-ተውባ የመጀመሪያዎቹን አንቀጾች ያነቡላቸውና የሺርክ ባለቤቶችንም ስምምነቶች ወደዚያ ይወረውሩላቸው ዘንድ ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብን ላኳቸው፡፡ እንደዚሁም አንድም አጋሪ (ሙሽሪክ) ከዚህ ዓመት በኋላ ሐጅ እንዳያደርግ መከልከሉንና ልክ በጃሂሊያው ዘመን ሲያደርጉ እንደነበረውም (በከዕባ ዙሪያ) እርቃን ሆነው ጠዋፍ ማድረግ መከልከሉን በማስመልከት በሰዎች መካከል ያውጁ ዘንድ (ላኳቸው)፡፡

## የስንብት ሐጅ

ከሂጅራ በኋላ በአስረኛው ዓመት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የስንብት ሐጃቸውን (ሐጅ-ጀቱል ወዳዕ) አደረጉ፡፡ ከተለያዩ ጎሳዎችና ከተማዎች የተውጣጡ ሙስሊሞች፣ ቁጥራቸው ከአንድ መቶ ሺ በላይ ሲሆኑ፣ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ወጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) የሐጅ አደራረግ ሥርዓትን አስተማሯቸው፡፡ ቀጣዩን የቁርኣን አንቀጽ በማንበብም በዐረፋ ዕለት ኹጥባ አደረጉ፡- *« …ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡ » (አል-ማኢዳ 5፡3)*

እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለታዳሚዎቻቸው አሁን ዷኑ መሟላቱን አሳውቋቸው፡፡ እነርሱንም በአላህ መጽሐፍና በመልዕክተኛው ሱንና አማካኝነት የመጣውን ነገር አጥብቀው እንዲያዙ መከሯቸው፡፡ በነርሱ መካከልም ደማቸውን፣ ገንዘባቸውንና ክብራቸውን እርም አደረጉ፡፡ ይህም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የስንብት ምክር መካከል ነበር፡፡

## የኡሳማ መላክ

በወርሃ ሰፈር ውስጥ ከሂጅራ በኋላ በአስራ አንደኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሩሞች ጋር ለመዋጋት የጦር ሠራዊትን አዘጋጁ፡፡ ኡሳማ ኢብን ዘይድንም የሠራዊቱ መሪ አድርገው ሾሙ፡፡ የጦር ሠራዊቱም ለጉዞ ወጣ፡፡ አል-ጁርፍ ዘንድም ካምፓቸውን ቀለሱ፡፡ ከዚያም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመታመማቸው ዜና ደረሳቸው፡፡

## የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎች ማጠቃለያ

**የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎችን፣ ልዑካንና ሠራዊትን የሚመለከት ማጠቃለያ**

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያካሄዷቸው ዘመቻዎች፣ ልዑካንን የመላክ ሥራዎችና ጦርነቶች በሙሉ የተካሄዱት ከሂጅራ በኋላ በአስር ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነበር፡፡ ያደረጉትን ጦርነትና የላኩትን ልዑካን ብዛት በተመለከተ እነርሱ በግምት ወደ ስድሳ የሚሆኑ ነበሩ፡፡ ያካሄዱትን ዘመቻዎች ብዛት በተመለከተ ሀያ ሰባት ነበሩ፡፡ ከነዚህ ዘመቻዎች መካከልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው በዘጠኙ ውስጥ ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህም በድር፣ ኡሑድ፣ አል-ኸንደቅ፣ አል-ቁረይዛ፣ አል-ሙስጠሊቅ፣ ኸይበር፣ የመካ መከፈት (አል-ፈትሕ)፣ ሑነይን እና ጧኢፍ ሲሆኑ፣ ከነዚህም ዘመቻዎች መካከል ከፊሎቹን የሚመለከቱ የቁርአን አንቀጾች ወርደዋል፡፡

**በቁርአን የተገለጹ ዘመቻዎች**

**የበድር ዘመቻ፡-** ሱረቱል አንፋል የወረደችው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ምዕራፍዋም ሱረቱ በድር በመባል ተሰይማለች፡፡

**የኡሑድ ዘመቻ፡-** የሱረቱ ኣሉ ዒምራን የመጨረሻው ክፍል፣ እንዲህ ከሚለው የኃያሉ አላህ ቃል አንስቶ *«ለምእምናቹም ለውጊያ ሥራዎችን የምታዘጋጅ ኾነህ ከቤተሰብህ በማለድክ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡»* - (3፡ 121) - እስከ ምዕራፉ መቋጫ አቅራቢያ የወረደችው ይህንኑ ዘመቻ አስመልክታ ነበር፡፡

**የኸንደቅ፣ የቁረይዛና የኸይበር ዘመቻዎች፡-** የሱረቱል አሕዛብ የመሀከለኛው ክፍል የወረደው እነዚኑ ዘመቻዎች አስመልክቶ ነበር፡፡

**የበኑ አን-ነዲር ዘመቻ፡-** ሱረቱል ሐሽር የወረደችው ይህንኑ ዘመቻ አስመልክታ ነበር፡፡

**የአል-ሑደይቢይ-ያ፣ የኸይበርና የአል-ፈትሕ (የመካ መከፈት) ዘመቻዎች፡-** ሱረቱል ፈትሕ እን አን-ነስር እነዚኑ ዘመቻዎች አስመልክተው የወረዱ ነበሩ፡፡

**የተቡክ ዘመቻ፡-** ከሱረቱ ተውባ የሆኑ የተወሰኑ አንቀጾች የተገለጹት ይህንኑ ዘመቻ በማስመልከት ነበር፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቆሰሉት በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን ያም የኡሑድ ዘመቻ ነበር፡፡ በበድር፣ በኡሑድና በሑነይን ዘመቻዎች ላይ መላኢኮች ከርሳቸው ጋር ሆነው ተዋግተዋል፡፡ በኸንደቅ (የጉድጓዱ) ዘመቻ ዕለት መላኢኮች ወርደዋል፡፡ሙሽሪኮችም ተንቀጥቅጠዋል፡፡ በረቀቀ ሁኔታ ተወግተው ተሸንፈዋል፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) በሙሽሪኮች ላይ ጠጠርን ወርወሩ፡፡ ስለሆነም እነርሱ ሸሹ፡፡ ታላቅ ድል የተገኘው በሁለት ዘመቻዎች ላይ ሲሆን እነርሱም በድርና ሑነይን ነበሩ፡፡ ‹አል-ሚንጀኒቅ› የተባለውን የጦር መሣሪያ ማስወንጨፊያን በመጠቀም የተዋጉት በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን እርሱም የጧኢፍ ዘመቻ ነበር፡፡ በተቆፈረ ቦይ አማካኝነት ምሽግን የያዙትም በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን እርሱም የአሕዛብ ዘመቻ ላይ ነበር፡፡ ይህንኑም ያመላከታቸው ሰልማን አል-ፋሪሲ (ረ.ዐ) ነበር፡፡

## መታመማቸውና መሞታቸው



ኃያሉ አላህ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዱንያ ላይ መቆየትን አልያም ከርሱ ጋር መገናኘትንና ጀነትን ይመርጡ ዘንድ ምርጫን አቀረበላቸው፡፡ ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጌታቸው ጋር መገናኘትንና ጀነትን መረጡ፡፡ ከዚያም በፅኑ ታመሙ፡፡ በዓኢሻ ቤት ውስጥ ያስታምሟቸው ዘንድ ከሚስቶቻቸው ፈቃድን ጠየቁ፡፡ እነርሱም ይህንኑ ፈቀዱላቸው፡፡ መስጂድ ገብተው ሰዎችን ማሰገድ በተሳናቸው ጊዜ አቡ በክር ሰዎችን እንዲያሰግዱ አዘዙ፡፡ ይህም ከርሳቸው በኋላ አቡ በክር ተተኪያቸው እንደሚሆኑ አንዳች ማረጋገጫን የሰጠ (ክስተት ነበር)፡፡

በዕለተ ሰኞ፣ በ12ኛው ቀን፣ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል፣ ከሂጅራ በኋላ በ11ኛው ዓመት ሰዎች የሱብሕ ሶላትን እየሰገዱ ሳሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደነርሱ ወጡ፡፡ እነርሱም እርሳቸውን እስከሚመለከቱ ድረስ መጋረጃው ተመለሰ፤ በሩም ተከፈተ፡፡ እናም ሶላታቸውን አሟልተው እንዲሰግዱ ምልክት ሰጧቸው፡፡ ለነርሱም ፈገግ አሉላቸው፡፡ ከዚያም ረፋዱ በበረታ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕይወታቸው አለፈች፡፡ የርሳቸው ሕልፈትም አማኞች ላይ ከደረሱ መከራዎች ሁሉ እጅግ ከባዱ ሆነ፡፡ በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሞት የተነሳ ሙስሊሞችም እጅግ የበረታ ሐዘንን አዘኑ፡፡ ከዚያም ሰዎች ወደ አቡ በክር ተሰባሰቡና በተተኪነትም (በኸሊፋነትም) የታማኝነት ቃል ኪዳናቸውን ሰጧቸው፡፡ በርሳቸው ተተኪነት ዙሪያም ከሰዎች መካከል አንድም አልተቃወመም ነበር፤ ምክንያቱም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ በእስልምና የቀደማቸውንና በተቀሩት ተከታዮች ላይ ብልጫ ያለው ሰው ማን እንደሆነ ሰዎቹ ያውቁ ነበርና፡፡

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጸደ ገላቸው ታጠበና በሦስት ነጫጭ ልብሶች አማካኝነት ተከፈኑ፡፡ ከዚያም በዚያው በሞቱበት ቦታ ላይ የሙእሚኖች እናት የሆነችው የዓኢሻ ቤት ውስጥ ተቀበሩ፡፡ ይህም ነብያትን በተመለከተ የአላህ ሱንና ሲሆን እነርሱም የሚቀበሩት በሞቱበት ቦታ ላይ ነው፡፡ ሁለቱም የሰው ዘርና ጋኔኖች የጌታችንን ሶላትና ሰላምን በርሳቸው ላይ ያወርዳሉ፡፡ እኛም እርሳቸው አማናቸውን እንዳደረሱ፣ ተከታዮቻቸውንም እንደመከሩና በአላህም መንገድ ላይ ተገቢውን ትግል እንዳረጉ እንመሰክራለን፡፡ ስለሆነም ነብይ በተከታዮቹ ሳቢያ ከሚመነዳው በላይ ኃያሉ አላህ በተከታዮቻቸው ሳቢያ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አብዝቶ እንዲመነዳቸው እንለምነዋለን፡፡ ምስጋና ሁሉ የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ይገባ፡፡

### ማጠቃለያ

ሐስ-ሳን ኢብን ሣቢት (ረ.ዐ)፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ገጣሚ የሆኑት እንዲህ ብለዋል፡-

ጌታ ሆይ! እኛን ከነብያችን ጋር አንድ ላይ ሰብስበን
በምቀኞች ዓይኖች በተወደሰች ጀነት ውስጥ ስንሆን
በጀነቱል ፊርደውስ ውስጥ፣ እርሷንም ለኛ ጻፍልን
የሞገሱ ባለቤት፣ የልዕልናና የታላቅነትም ባለቤት አንተ ነህና
አላህና በዐርሹ ዙሪያ ያሉ በርሳቸው ላይ ሰለዋትን ያወርዳሉ
መልካሞቹም ለተባረከው አሕመድ ሰላምታቸውን ያደርሳሉ፡፡

# 3ኛው ፈተና

| ውሸት | እውነት | ጥያቄዎቹ |
|---|---|---|
|  | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ) ፍዮሎችን ማገዳቸው ትዕግስት እንዲኖራቸውና ለደካሞችም እንዲያዙ፤ እነርሱንም የመጠበቅ ኃላፊነት እንዲወስዱ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ ነበር |
|  | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 40 ዓመት ሲሞላ የነብይነት ብርሃኑ ከርሳቸው ላይ ደምቆ ነበር፡፡ አላህም ከርሱ በሆነ መልዕክት በዕለተ ጁምዓ ላይ አላቃቸው፡፡ |
|  | £. | ከቁረይሾች በኩል በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሲደርስ የነበረው ስቃይ ይበልጡኑ በረታ፡፡ እርሳቸውንና አህሉል በይትንም በአቡ ጣሊብ ተራራማ መንገድ (ሽለቆ) ውስጥ ለ3 ዓመታት አገቷቸው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 49 ዓመት ሲሞላ ከእገታው ሰብረው ወጡ፡፡ |

1. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካ ውስጥ የተወለዱት፡- ሀ/ በዝሆን ዓመት ለ/ ከሂጅራ በፊት በ53 ዓመታት ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
2. መለኮታዊ ራዕዩ መገለጽ ሲጀምር፡- ሀ/ እርሳቸው ዘንድ ገለልተኝነት ተወዳጅ ተግባር ተደርጎ ነበር ለ/ የመጣው እንደ መልካም ሕልም ሆኖ ነበር ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
3. መለኮታዊ ራዕዩ ስንት ደረጃዎች አለው? ሀ/ 5 ለ/ 7 ሐ/ 3
4. የደዕዋቸው እርከኖች፡- ሀ/ 2 ነበሩ ለ/ 3 ነበሩ ሐ/ 5 ነበሩ
5. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ አል-አቅሷ በሌሊቱ ክ/ጊዜ በነፍሳቸውና በሥጋቸው ተወሰዱ፡፡ ከዚያ ከሰማያት በላይ በ .............. ወደ ኃያሉ አላህ ተወሰዱ፡፡ አላህም አናገራቸው፡፡ አምስት ወቅት ሶላቶችንም ግዴታ አድርጎ ደነገገባቸው፡፡ ሀ/ በሥጋቸው ለ/ በነፍሳቸው ሐ/ በሥጋቻውና በነፍሳቸው
6. በእስልምና ውስጥ የመጀመሪያው መስጂድ፡- ሀ/ አል-ሐራም ለ/ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ሐ/ አል-አቅሷ መ/ ቁባእ
7. የቂብላው አቅጣጫ የተቀየረው፡- ሀ/ በመካ ውስጥ ከሂጅራ በፊት ለ/ ከሂጅራ በኋላ በ2ኛው ዓመት ለ/ ከሂጅራ በኋላ በ3ኛው ዓመት
8. በወርሃ ረመዷን ውስጥ የተካሄደው የበድር ጦርነት በስንተኛው ዓመት ነበር? ሀ/ ከሂጅራ በኋላ በ2ኛው ዓመት ለ/ ከሂጅራ በኋላ 3ኛው ዓመት

| አቡ በክር አስ-ሲድቅ | ዘይድ ኢብን ሓሪሓ | ቢላል ኢብን ረባሕ | ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ | በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ለማመን ቀዳሚዎቹ፡- |
|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ |  | ከወንዶች |
| £ | £ | £ |  | ከታዳጊዎች |
| £ | £ | £ |  | ከአገልጋዮች |
| £ | £ | £ |  | ከባሮች |

| 7 ዓመት | ዐብደሏህ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ | ወደ 8 ዓመት | ዐብዱል ሙጠሊብ | አቡ ጧሊብ | የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሳዳጊዎች፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | ከእናታቸው ሞት በኋላ አያታቸው ....... |
| £ | £ | £ | £ | £ | አያታቸው ሲሞቱ ዕድሜያቸው ...... |
| £ | £ | £ | £ | £ | ከዚያም አጎታቸው ....... አሳደጓቸው |
| £ | £ | £ | £ | £ | ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተረግዘው ሳሉ አባታቸው .... ሞቱ |
| £ | £ | £ | £ | £ | እናታቸው ስትሞት ዕድሜያቸው ...... ነበር |

| 1 ዘመቻ | 9 | 27 | 60 | 10 ዓመት | ዘመቻዎቻቸውና ልዑካኖቻቸው፡- |
|---|---|---|---|---|---|
| £ | £ | £ | £ | £ | ሁሉም ዘመቻዎችና ልዑካኖች የተካሄዱት ከሂጅራ በኋላ .... ዓመት ውስጥ ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | የጦራና የልዑካናቸው ቡድን ብዛት በግምት ..... ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | በጥቅሉ ....... ዘመቻዎች ተካሄደዋል |
| £ | £ | £ | £ | £ | የተሳተፉባቸው ዘመቻዎች ብዛት ..... ነበር |
| £ | £ | £ | £ | £ | የቆሰሉበት ዘመቻ ...... ነበር |

## ደስተኛ ሕይወትን ለመምራት የሚረዱ መንገዶች

ጸሐፊው፡- ዐብዱር ረሕማን ኢብን ናሲር አስ-ሲዕዲ (1307 – 1376 ዓ.ሂ)፣ በዘመናቸው እጅግ ጉልህ ከሆኑ የሙስሊም ልሀቃን መካከል አንዱ ሲሆኑ፣ (በዕውቀታቸው) የኢስላማዊ ዕውቀትን መሠረተ ሐሳብ ከያዙ ኢማሞች መካከልም ተጠቃሹ ናቸው፡፡

ይህንኑ መጣጥፍን ያዘጋጁበት ምክንያት ቢኖር ሸይኹ ለሕክምናዊ ዓላማ (በ1373 ዓ.ሂ) ወደ ሊብናን በሚጓዙበት ጊዜ «ጭንቀትን እንዴት እንደምናቆምና ትክክለኛ ሕይወትን እንዴት መኖር እንደምንጀምር» የተሰኘውንና በዴል ካርኒጌ የተዘጋጀውን መጽሐፍ አንብበው በይዘቱም ስለተማረኩ ነበር፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ጭብጥን የያዘ መጽሐፍን ለማዘጋጀት በቁ፡፡ ቀጥሎ የሚቀርቡ 22 ነጥቦችም ወደ ደስተኛ ሕይወት ይመራሉ ተብለው በርሳቸው የተዘረዘሩ ናቸው፡-

1/ በኃያሉ አላህ ማመንና መልካም ተግባራትን መሥራት፡- እምነት ኃያሉ አላህ ባዘዘው ነገር ላይ ትዕግስት፣ ደስታና እርካታ እንዲኖርህ ወደዚያ ይመራሀል፡፡

2/ በንግግርና በተግባርም ለመላው ፍጡራን ደግ መሆን፤ ምክንያቱም መልካምነት መልካምነትን ያስገኛል፤ ከፋትንም ይገፈትራልና፡፡

3/ ራስን በመልካም ተግባራትና በጠቃሚ ዕውቀት ላይ ቢዚ ማድረግ፡- ይህም ልብን ስለሚያስጨንቁህ ነገሮች የማሰብ አሉታዊ ትኩረትህን ያዘርልሀል፡፡

4/ አስተሳሰብህን በዕለታዊ ሥራዎችህ አማካኝነት ቢዚ ማድረግ፡- ስለሆነም ባለፈው ነገር አታዝንም፤ ስለሚመጣውም አትጨነቅም፤ ምክንያቱም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጭንቀትና ከሐዘን በአላህ ይጠበቁ ነበርና፡፡

5/ አላህን በማውሳት ላይ ተጨማሪ ማውሳትን ማድረግ፡- ምክንያቱም አላህን አብዝተው ማውሳት ለልብ እርካታንና ስክነትን ያስገኛልና፡፡

6/ የአላህን የሚታዩና የማይታዩ (ግልጽና ስውር) ፀጋዎችን መዘርዘር፡- ምክንያቱም ይህ ምስጋናን የሚያስገኝና ትካዜንም የሚያስወግድ ተግባር ነውና፡፡

7/ ካንተ በታች ያለውን ሰው መመልከት ላለህ ነገር አላህን እንድታመሰግን ሲያደርግህ፣ በሌለህ ነገርም ከመተከዝና ከማዘን ያድንሀል፡፡

8/ ያለፈውን ነገር መርሳት፤ ምክንያቱንም ያለፈውን ነገር ዳግም መልሰህ ልታገኘው አትችልምና፡፡ ስለሆነም ራስህን በዚያ ላይ ቢዚ ማድረግ ትርጉም የለሽና ከንቱነት ነው፡፡

9/ ወደ አላህ ዱዓ ማድረግ፡- ለምሳሌ ያህል ኃያሉ አላህ እምነትህን፣ ዓለማዊ ጉዳዮችህንና የቀጣዩ ዓለም ጉዳዮችህንም እንዲያስተካክልልህ (እንዲያሳምርልህ) መለመን - ይህም ልክ በሐዲሥ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ነው፡፡

10/ በአደጋ ጊዜ እጅግ ከባድ የሆነውንም ጉዳት መጠበቅ፤ ምክንያቱም ከደረሰው በላይ የባሰ መጥፎ ነገር ሊከሰት እንደሚችል ማሰብ በአነስተኛ ጉዳት ሳቢያ የመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖን ይቀንሳል፡፡

11/ በከንቱ ስሜትና በምናባዊነት ተገፋፍተው ከአቅም በላይ አለማሰብ፤ ምክንያቱም ከንቱ ስሜት መጥፎ አስተሳሰቦችን ያመርታል፤ አንተም በአሉታዊነት እንድትሞላ ያደርግሀል፤ ይህም የጭንቀትና የሕመም መንስኤ ይሆናል፡፡

12/ በአላህ ላይ መተማመንና በርሱም ላይ መመካት፡- «በአላህ ላይ ለሚመካ ሰው አላህ ለርሱ በቂው ነው፡፡» (65፡3)

13/ የሌሎች ሰዎችን ደካማ ጎኖች መቀበልና እነርሱ በሚያደርሱብህ ጉዳይ ላይ ትዕግስት ማድረግ፡- እያንዳንዱ ሰው ደካማ ጎን (ጉድለት) አለው፤ ወይም እኛ የማንወዳቸውን ነገሮች ሊፈጽሙብን ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ከነርሱ አሉታዊ ጎን ይልቅ አዎንታዊ ጎናቸውን ተመልከት ተገቢ ነው፡፡

14/ ራስን በማይረቡ ነገሮች ቢዚ አለማድረግ፡- ልክ አንተ ከአደጋዎች ጋር መኖር እንደማትፈልግ ሁሉ ራስህን በከንቱ ጉዳዮችም ማስጨነቅ የለብህም፡፡ ራስህን ከከንቱ ጉዳዮች የማራቅ ምርጫውም በእጅህ ነው፡፡

15/ ሕይወት አጭር ናት፡፡ እናም እውነተኛው ሕይወት (ምንም እንኳን) አጭር ብትሆንም የደስታና የእርካታ ሕይወት ናት፡፡ ስለሆነም ሕይወትን በጭንቀትና በሐዘን (የበለጠ) አታሳጥራት፡፡

16/ ለአብዛኞቹ ስጋቶችህ ምንም የተጨበጠ ማስረጃ የለህም፡፡ በእውነቱ አንተ የምትጨነቅላቸው አብዛኞቹ ነገሮች ገና አልተከሰቱም፡፡ ስለሆነም ገና ያልተከሰቱ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የሚችሉትን እንዲያደበዝዙ አትፍቀድላቸው፡፡

17/ ሰዎች በሚያወሩት ነገር አትጨነቅ፤ ምክንያቱም የሰዎች ሐሜት በራሳቸው ላይ ነውና፡፡ የሆነ ሆኖ አንተ በነርሱ ራስህን ቢዚ ካደረክ፣ ከዚያም ልክ እነርሱ ራሳቸውን እየጎዱ እንዳሉት ሁሉ አንተም ራስህን ትጎዳለህ፡፡

18/ ሕይወትህ አስተሳሰቦችህን ትከተላለች፡፡ ስለሆነም አስተሳሰቦችህ ለሃይማኖትህ ወይም ለዓለማዊ ጉዳዮችህ ጠቃሚ ከሆኑ፣ ከዚያም አንተ ደስተኛ የሆነ ሕይወት ይኖርሀል፡፡ የረካህም ትሆናለህ፡፡ አለበለዚያ ግን ተቃራኒው ይከሰትብሀል፡፡

19/ ለነዚያ ካንተ ላይ ሙብት ላላቸው ሰዎች ወይም ለነዚያ ባንተ ላይ ሙብት ለሌላቸው ሰዎችም መልካም ነገርን ስትሠራ ከነርሱ ምስጋና አትጠብቅ፡፡ የዚያኔ ይህ ባንተና በአላህ መካከል የሚደረግ ንግድ ይሆንልሀል፡፡ ስለሆነም የሰዎች ምስጋና ካንተ መቅረት አያስጨንቅህ፡፡

20/ በዚያ አንተን ተጠቃሚ በሚያደርግህ ነገር ላይ ራስን ቢዚ አድርግ፤ ምክንያቱም ጎጂ ጉዳዮች ትካዜንና ሐዘንን ያስከትላሉና፤ ስለሆነም በጠቃሚ ተግባራት በኩል እገዛን ፈልግ፡፡

21/ ጉዳዮችህን በወቅታቸው ለመጨረስ ትጋ፤ ምክንያቱም የዘገዩ ጉዳዮች ከመጪ ጉዳዮችህ ጋር ሆነው ባንተ ላይ ይወዘፉና አንተም በነርሱ አስቀድመህ የተዋጥክ ትሆናለህ፡፡

22/ ጉዳዮችህን በቅደመ ተከተል አስቀምጣቸው፤ ከዚያም እጅግ ጠቃሚ ከሆነ ጀምር፡፡ ከዚያም ቀጥሎ በጣም አስፈላጊ የሆነውን አስከትል፡፡ ከሙያም ረገድ ያንን አንተ ይበልጥ ያዘነበልክብትን ምረጥ፡፡ በዚህም አንተ በብስጭት ወይም በስልቹነት ውስጥ አትወድቅምና፡፡ እንደዚሁም ምክርን ጠይቅም፤ ምክንያቱም ምክርን ስትጠይቅ አትፀፀትምና፡፡

# ማውጫ


- መግቢያ ........................................ 3
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መገለጫ ባህሪያት ........................................ 5
- የመጀመሪያው ፈተና ........................................ 13
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምሪት ........................................ 15
- ሁለተኛው ፈተና ........................................ 20
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መለያ ባህሪያት ........................................ 23
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች ........................................ 26
- ከነብይነታቸው በፊት ........................................ 31
- የራዕዩ ጅማሮ ........................................ 33
- የመካው ምዕራፍ ........................................ 36
- የመዲናው ምዕራፍ ........................................ 39
- የዘመቻዎቻቸው አጭር ማጠቃለያ ........................................ 46
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መታመምና መሞት ........................................ 47
- ሦስተኛው ፈተና ........................................ 48
- ደስተኛ ሕይወትን ለመምራት የሚረዱ መንገዶች ........................................ 51
- ማውጫ ........................................ 53